# ኢፕድ አዲስ ዘመን

ረቡዕ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 261 ግንቦት 21 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!












# የፕሪቶሪያው ስምምነት አተገባበርና ቀጣይ የቤት ሥራዎች

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

ለሰሜኑ ደም አፋሳሽ ጦርነት እልባት የሰጠው የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ከተፈረመ ዓመት ከመንፈቅ አስቆጥሯል። ስምምነቱ በኢትዮጵያ መንግሥትና በህወሓት መካከል ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ መፈረሙ ሲሰማ ለብዙዎች የህሊና እረፍት ሰጥቷል።

ከምንም በላይ ደግሞ ስምምነቱት ተከትሎ የየተገበረው ተኩስ አቁም በትግራይ፤ በአማራና አፋር ክልሎች የሚኖሩ ዜጎችን ከሰቀቀን የታደገ ፤ ስቃይና መከራቸውን ያስቆመ ለመሆን በቅቷል። በርካታ

የፕሪቶሪያው ስምምነት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ሕገ-ወጥ የትምህርት ማስረጃ ኢኮኖሚያዊ ተፅዕና እያሳደረ ነው

ገጽ 4


አቶ መሬሳ ፊጤ

## 89 ሺህ ተፈናቃዮች ወደ ቀያቸው ተመልሰዋል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- 89ሺህ ተፈናቃዮች ወደ ቀያቸው መመለሳቸውን የሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን አስተዳዳሪ አቶ መሬሳ ፊጤ ገለጹ።

የዞኑ አስተዳዳሪ አቶ መሬሳ ፊጤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዞኑ በጽንፈኞች ላይ ርምጃ

89ሺ ተፈናቃዮች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የውጭ ኢንቨስተሮች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ለ75 ሺህ ሰዎች የሥራ እድል ፈጥረዋል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት ባለፉት አስር ወራት የውጭ ኢንቨስተሮች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ለ75 ሺህ ለሚጠጉ ሰዎች የሥራ እድል መፍጠራቸውን የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ። ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት ለመሳብ ስምንት ቢዝነስ ፎረሞች መካሄዳቸውን ገልጿል።


የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሐና አርዓያ ሥላሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተያዘው በጀት ዓመት እስካሁን ድረስ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ብቻ ለ75 ሺህ ለሚጠጉ ሰዎች የሥራ እድል ተፈጥሯል። ሥራ ዕድሉም የተፈጠረው የውጭ ኢንቨስተሮች ኢንቨስት ባደረጉባቸው የኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ነው።

ኮሚሽነሯ ፤ በተለይ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ከተቋቋሙ ወዲህ ከሥራ እድል ፈጠራና የገቢና ወጪ

... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





## የቀድሞ ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋዜጠኛ ፋንታሁን ኃይሌ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋዜጠኛ ፋንታሁን ኃይሌ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። ጋዜጠኛ ፋንታሁን ኃይሌ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የስፖርት አምድ አዘጋጅ በመሆን ሠርቷል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ለጋዜጠኛው ቤተሰቦች ወዳጅ ዘመዶችና የሥራ ባልደረቦቹ መጽናናትን ይመኛል።

# ርዕሰ መስተዳድር

## አቶ ጥላሁን ከበደ የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎትን አስጀመሩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተደድር አቶ ጥላሁን ከበደ "በጎነት ለኢትዮጵያ ከፍታ" በሚል መሪ ቃል የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎትን በወላይታ ሶዶ ከተማ አስጀምረዋል።

ርዕሰ መስተደድሩ በወላይታ ሶዶ ከተማ የአቅመ ደካሞች ቤት የማደስ ፕሮግራም አከናውነዋል። የሁለት አቅመ ደካሞች ቤት ሙሉ በሙሉ በርዕሰ መስተዳድሩ ወጪ እንደሚሸፈን ተገልጿል።

ርዕሰ መስተደድሩ በጎነት ለኢትዮጵያ ከፍታና ለራስ በመሆኑ ሁሉም በዚህ የበጎ ተግባር አገልግሎት መሳተፍ አለበት ብለዋል። የበጎ ተግባር አገልግሎት የህሊና እርካታ ከማስገኘቱ ባሻገር የዜጎችን ሕይወት ያሻሽላል ያሉት አቶ ጥላሁን ባለሀብቶችና ሌሎችም ግለሰቦች መሳተፍ ይኖርባቸዋል ብለዋል።

ወጣቶች እና ሌሎችም የህብረተሰብ ክፍሎች በክረምት በበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንዲሳተፉ ጥሪ አቅርበዋል። በተለይም ታዳጊ ወጣቶች ይህን ተግባር የሕይወታቸው መርህ እንዲያደርጉ አሳስበዋል። አመራሩም ህብረተሰቡን በማስተባበር የተቸገሩትን የመርዳት ሥራ በቋሚነት ባህል ሆኖ እንዲቀጥል መሥራት አለባቸው። በዚህ የበጎ አገልግሎት ተግባር ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች የሃይማኖት አባቶች የድርሻቸውን እንዲወጡ አሳስበዋል።

የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሳሙኤል ፎላ በበኩላቸው በጎ ፈቃድ አገልግሎት ከማህበራዊ ኃላፊነት አንዱ መሆኑን ገልጸው ይህን የህሊና ዕርካታ የሚሰጠውን አገልግሎት በተለያዩ ዘርፎች አቅመ ደካሞችን በማገዝ ችግኝ በመትከል፣ ደም በመለገስ፣ የትምህርት አገልግሎትንና ሌሎችን አገልግሎት መስጠት ያስፈልጋል ብለዋል።

በዚህም የበጎ ተግባር መላውን የዞኑን ህዝብ በማስተባበር ብልጽግናን ማሳካት ይኖርብናል። የሶዶ ከተማ ከንቲባ ጀገና አይዛ በበኩላቸው የመረዳዳትና የመተሳሰብ ባህላችንን በማጎልበት አቅመ ደካሞችን በመርዳት የበጎ ተግባር ሥራዎችን በማከናወን ሁሉም የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ጠይቀዋል።

በመድረኩ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጥላሁን ከበደን ጨምሮ የክልሉ የመንግሥት ዋና ተጠሪ አቶ አለማየሁ ባውዲ፣ የክልሉ ከፍተኛ አመራሮች፣ የወላይታ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሳሙኤል ፎላ የሶዶ ከተማ ከንቲባ ጀገና አይዛ የሀገር ሽማግሌዎች መገኘታቸውን ከክልሉ ኮሚኒኬሽን ቢሮ የተገኘው መረጃ አመልክቷል።

# የሥራ ፈጠራ ተግዳሮቶችና ማስፈያ መንገዶች

**መስከረም ሰይፉ**
**ዜና ሐተታ**



በየዓመቱ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተመርቀው ይወጣሉ። እነዚህ ወጣቶች የመጀመሪያ ፍላጎታቸው በተማሩበት የትምህርት መስክ ወደ ሥራው ዓለም መቀላቀል ቢሆንም ለበርካቶች ይህ ዓላማ በነበር ብቻ ሲቀር ይስተዋላል። አንዳንዶች የእራሳቸውን ሥራ ፈጥረው ገንዘብ ማግኘት ሲጀምሩ ሌሎች ግን በሥራ ጠባቂነት ብቻ ጊዜያቸውን ያባክናሉ።

በዚህ የተነሳ መንግሥት ለሁሉም ወጣት የሥራ እድል ማቅረብ ስለማልችል ወጣቶች ሥራ ፈጣሪ ቢሆኑ እመክራለሁ ሲል ይደመጣል። ለመሆኑ የመንግሥት የሥራ እድል ሳይጠብቁ በራሳቸው ተፍጨርጭረው ሥራ ለመጀመር የሚሞክሩ ወጣቶች የሚያልፉበት መንገድ ምን ይመስላል ? በዚህ ጉዳይ ላይ የሚመለከተው የመንግሥት አካልስ ሥራ ፈጣሪዎችን ለማበረታት ምን እየሠራ ይገኛል?

ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሃሳቡን የሰጠው ወጣት ሰሚር አብደላ፤ በአካውንቲግና ፋይናንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ቢኖረውም ሥራ ማግኘት ሳይችል ከአንድ ዓመት በላይት ቤት ውስጥ ማሳለፉን ይገልጻል።

የሥራ አጥ መታወቂያ እሱ ከሚኖርበት ወረዳ አውጥቶ ቢደራጅም ምንም አይነት ድጋፍ ባለማግኘቱ ምክንያት ከቤተሰብ ብር ተበድሮ አነስ ያለች ቁርስ ቤት ለመክፈት ቢሞክርም እሱ ባለው የገንዘብ አቅም የሚከራይ የንግድ ቤት ማጣቱን ያስታውሳል። ኪራያቸው ዝቅተኛ የሆኑ ቦታዎች ከፍተኛ ብር ለቁልፍ ሽያጭ እየተባለ የሚጠየቅባቸው መሆኑንም ያነሳል።

በዚህ ሳቢያም ተንቀሳቃሽ ቤት በመሥራት በጎዳናዎች ቀለል ያሉ ምግቦችን እየሠራ ለመሸጥ ቢሞክርም የተለያዩ መጉላላቶች ያጋጠሙት በመሆኑ ሥራውን ማቆሙን ያስረዳል።

ወጣት ሰሚር ወጣቶች የሥራ እድል ፍጠሩ ሲባል በተለያዩ ሚዲያዎች የሚሰማ ቢሆንም ብድርና ቦታ ማግኘት ቀላል አይደለም ይላል።

ሌላኛው ስሙን መግለጽ ያልፈለገ የአዲስ አበባ ነዋሪ ወጣት እንደገለጸው የሜካኒካል ኢንጂነሪግ ተመራቂ ሲሆን ከዩኒቨርሲቲ ባገኘው ትምህርት ከጓደኞቹ ጋር በመሆን በግብርና ዘርፉ ያሉ ችግሮች ሊያቃልል የሚችል ማሽን መሥራት ችለዋል።

የሠሩንት ማሽን ወደ ገበሬው በመውሰድ ባደረጉት ምልከታ ከፍተኛ ይሁንታ ያገኘ ቢሆንም ማሽኑን አባዝቶ ተደራሽ ለማድረግ የገንዘብ እጥረት እንዳጋጠማቸው ይናገራል። ለዚህም የተለያዩ የመንግሥት እንዲሁም የግል ተቋማት ቢሮችን ቢያንኳኩም የብድርም ሆነ የድጋፍ መልስ እንዳልተሰጣቸው ይናገራል።

ወጣቱ አዲስ የሥራ ሃሳብ ያላቸው በርካታ ወጣቶች ይኖራሉ ነገር ግን ወጣቱን ሥራ ፍጠር ከማለት በስተቀር ወጣቱን ወደ ሥራ መፍጠር የሚገፋፋው ምቹ ሁኔታ አልተፈጠረም ሲል ሃሳቡን ይገልጻል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ደርጅት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራና ክህሎት ቢሮ ከሚፈጥረው የሥራ እድል በተጨማሪ በራሳቸው ሥራ ለመፍጠር የሚሞክሩ ወጣቶችን በማበረታት ረገድ ምን እየሠራ ይገኛል ሲል ጥያቄውን አንስቷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራና ክህሎት ቢሮ የሥራ ስምሪት ዳይሬክተር ሰብሀዲን ሱልጣን እንደገለጹት ፤መንግሥት ቋሚ የሥራ እድል መፍጠር ላይ ትኩረት አድርጎ ቢሠራም በራሳቸው ስራ ለመፍጠር የሚሞክሩ ወጣቶችን ለማበረታት ከተለያዩ ተቋማት ጋር እየሠራ ይገኛል ይላሉ።

አቶ ሰብሀዲን ወጣቶች በመጀመሪያ የሚያነሱት የብድር አቅርቦት እጥረት ለመፍታት አዲስ ካፒታል እንዲሁም አዲስ ብድርና ቁጠባ ከተባሉ ተቋማት ጋር የትምህርት ማስረጃን እንዲሁም ጨረታ ዋስትናን እንደማስያዣ እየተጠቀሙ ብድር እንዲሰጡ ከስምምነት በመድረስ ወደ ሥራ መገባቱን ይገልጻል።

ነገር ግን ወጣቱ መስራት የሚፈልገውና የሚጠይቀው የገንዘብ አቅም የማይመጣጠንበት ሁኔታ መኖሩን አንስተው፤ ቦታን በተመለከተ ለተወሰኑ ለሚደራጁ አካላት የሚሰጥ ቢሆንም ለሁሉም መሥሪያ ቦታና ገንዘብ ለመስጠት የሚያስችል አቅም የለም ሲሉ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

# በቤኒሻንጉል ክልል ለአረንጓዴ ዐሻራ 57 ሚሊዮን ችግኞች እየተዘጋጁ ነው

## በአንድ ጀምበር ከ10 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል ታቅዷል

**ማርቆስ በላይ**



አዲስ አበባ፡- በክልሉ ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ የሚውሉ ከ57 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን በአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ለመትከል ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በአንድ ጀምበር ከ10 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል መታቀዱም ተገልጿል።

በቢሮው የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ዳይሬክተር አቶ ፍቃዱ ደሳለኝ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ የሚውሉ ከ57 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን በዘንድሮው በአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ለመትከል ታቅዶ እየተሠራ ነው።

ለመጪው ክረምት ለሚካሄደው የአረንጓዴ ዐሻራ ልማት በሁሉም የክልሉ ወረዳዎች የተለያዩ ችግኞችን የማዘጋጀት ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ዘርፍ ከ57 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን በላይ ችግኝ ለማዘጋጀት ታቅዶ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ለመርሃግብሩ እስካሁን ከ32 ነጥብ አራት ሚሊዮን በላይ የተለያዩ ችግኞች የተዘጋጁ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ቀሪ ችግኞችን ለክረምቱ መርሃግብር ለማድረስ የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኙም ገልጸዋል።

በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች ላይ በሚገኙ 75 ጣቢያዎች ችግኞችን የማዘጋጀት ሥራ እየሠሩ እንደሚገኙ ጠቁመው፤ ለደን፣ ቀርከሃ፣ ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ችግኞች እየተዘጋጁ እንደሚገኙ ተናግረዋል።

ችግኞችን በአንድ ጀምበርና በክረምት ለሚካሄደው ችግኝ ተከላ አስፈላጊው ዝግጅት እየተካሄደ መሆኑን የገለጹት አቶ ፍቃዱ፤ የአንድ ጀምበር መርሃግብር ለሚካሄድባቸው ቦታዎች ካርታ በማዘጋጀት ከ10 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል ታቅዷል ብለዋል።

በመርሃግብሩ ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች የሚሳተፍበት ሲሆን ከ249 ሺህ በላይ አባወራዎች ተሳታፊ ይሆናሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ጠቁመው፤ ችግኝ ተከላው ከ46 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት ላይ እንደሚካሄድ አስረድተዋል።

የአረንጓዴ ዐሻራ የክልሉን የደን ሽፋንን ሥነ ምህዳር በማሳደግ በአፈርና ውሃ ጥበቃ ላይ የተሻለ ውጤት እያስገኘ እንደሚገኝም ገልጸዋል።

ከችግኝ ዝግጅቱ ጎን ለጎን የመትከያ ቦታ የመለየት ሥራ እየተከናወነ ቢሆንም በሚፈለገው ልክ እንዳልተሠራ ገልጸው፤ በየደረጃው የሚገኙ የሚመለከታቸው አካላት ቀጣይ ቀሪ ሥራዎችን በፍጥነት ማጠናቀቅ እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

በተጨማሪም ቡና፣ ፍራፍሬና የተለያዩ ችግኝ አይነቶችን የማዘጋጀት ሥራዎች በሌሎች የግብርና ዘርፎች ላይ እየተካሄደ መሆኑንና በሀገር አቀፍ ደረጃ የታሰበውን እቅድ ለማሳካት የሚያስችሉ ዝግጅቶች እየተካሄዱ እንደሚገኝም ጠቁመዋል።

# በትግራይ ክልል 70 ሚሊዮን ችግኞች ለመትከል ዝግጅት እየተደረገ ነው

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ ፡- በዘንድሮው ክረምት በትግራይ ክልል 70 ሚሊዮን የተለያዩ ችግኞች ለመትከል በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ የክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ አስታወቀ።

በክልሉ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ተስፋይ ተክለሃይማኖት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በክልሉ በዘንድሮው ክረምት ወቅት የሚተከሉ በ145 የችግኝ ጣቢያዎች ላይ የተለያዩ ችግኞች እየተዘጋጁ ነው፤ ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ ችግኖች ፍራፍሬ እና የእንስሳት መኖን ያካተቱ ናቸው።

እስከ አሁን ድረስ ከስድስት ሚሊዮን በላይ የችግኝ መትከያ ጉድጓዶች ተቆፍረው መዘጋጀታቸውን ገልፀው፤ ጦርነቱ ደን ሀብት ላይ ጉዳት በማስከተሉ ዘንድሮ በሚካሄደው የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ሕዝቡ በግል እና በጋራ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርግ ቅስቀሳ እየተደረገ ነው ብለዋል።

በሁሉም የትግራይ ገጠር ወረዳዎች እና ከተሞች ችግኝ ለመትከል ዕቅድ መያዙን ጠቅሰው፤ የበጀት እጥረት ቢያጋጥምም እስከ አሁን 50 በመቶ አካባቢ ሥራዎች መከናወናቸውን ገልፀዋል።

ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ በክልሉ ከዚህ ቀደምም በተለያየ ወቅት ችግኝ መትከል እና የተፈጥሮ ሀብት በመጠበቅ ይታወቃል። አሁን ላይ ግን እንደ ከዚህ ቀደሙ ችግኝ ተተክሎ ዘወር ማለት ሳይሆን በየጊዜው መንከባከብ እንደሚገባ ለማድረግ ሥልጠናዎች እየተሰጠ ነው።

ለመትከል ከተዘጋጁት ችግኞች መካከል በአብዛኛዎቹ የሀገር በቀል ዛፎች መሆናቸውን ገልጸው፤ከእነዚህ መካከልም ወይራ፣ ፅድና ዋንዛ እንደሚገኙበት ጠቅሰዋል። ይህም የተደረገበት ምክንያት በመጥፋ ላይ



ያሉ ሀገር በቀል ዝርያዎች ለማስፋፋት እና ወደ ነበሩበት ለመመለስ ታስቦ የተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

ህብረተሰቡ ከዚህ ቀደም በመዋቅር ተደራጅቶ የልማት ሥራዎች ሲሠራ መቆየቱን በማስታወስ፤ አሁንም የሚተከለው ችግኝ በጥንቃቄ እና በኃላፊነት ለመትከል ዝግጅት እያደረገ ነው ብለዋል።

ቀጣይ ሳምንት ባለሙያዎች ስለ ችግኝ ተከላ መርሃ ግብሩ ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ እንደሚያካሂዱም ገልፀዋል።

ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ ህብረተሰቡ እስከ አሁን አካባቢው ሲያለማ ቆይቷል፤ ዘንድሮው በሚደረገው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር በንቃት መሳተፍ ይኖርበታል።

በተለይ አመራሩ እስከ ወረዳ ድረስ ሕዝቡን በማደራጀት እና በማሳተፍ፤ ውጤታማ ሥራ መሥራት ይጠበቅበታል። የግብርና ባለሙያውም በአካል ቦታው ድረስ በመገኘት የራሱን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከት አለበት ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።



ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ

# ኤክስፖው

## የኮንስትራክሽን ዘርፉ ተዋንያን እድሎችና ተግዳሮቶችን እንዲገነዘቡ እድል ይፈጥራል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ ፡- ኤክስፖው የኮንስትራክሽን ተዋንያንን በማገናኘት ኢትዮጵያውያን የዘርፉን እድሎችና ተግዳሮቶች እንዲገነዘቡ እንደሚያስችል የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ። ዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን አውደ ርዕይ (ኤግዚቢሽን) ከግንቦት 22 እስከ 24 ቀን 2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ እንደሚካሄድም ተገልጿል።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ ለጋዜጠኞች ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን አውደ ርዕይ ከግንቦት 22 እስከ 24 ቀን 2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ ይካሄዳል። ይህም የኮንስትራክሽኑን ዘርፍ ተዋንያን በማገናኘት ኢትዮጵያውያን የዘርፉን እድሎችና ተግዳሮቶች እንዲገነዘቡ እድል ይፈጥራል።

የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ እድገት መገለጫው የኮንስትራክሽን ልማት ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በግንባታ ሂደት እድገት ውስጥ እያለፈች ነው ብለዋል።

አውደ ርዕይው የዘርፉን ልማት ወደ ፊት ማራመድ የሚችል አቅም ለሀገሪቱ መፍጠር እንደሚችል ጠቅሰው፤ የፈጠራ ሥራዎችን ጨምሮ ከግንባታ ማዘመን እስከ አገልግሎት ያሉ አጠቃላይ የዘርፉን ሂደት የሚያሳይ እንደሚሆን ገልጸዋል።

በአውደ ርዕይው በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሠማሩ ከ156 የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ድርጅቶች እንደሚሳተፉ ገልጸው፤ እስካሁን ከ5 ሺህ በላይ ጎብኚዎች በኦንላይን የተመዘገቡ ሲሆን በርካቶች እንደሚጎበኙት እንደሚጠበቅ ተናግረዋል።

መድረኩ የኮንስትራክሽን ተዋንያኖች በማገናኘት ኢትዮጵያውያን የዘርፉን እድሎችና ተግዳሮቶች እንዲገነዘቡ ማድረግ እንደሚያስችል አመልክተው፤ በዘርፉ የካበተ ልምድ ካላቸው ሀገራት ጠቃሚ ልምዶች የሚወሰድበት እንደሚሆንም አስረድተዋል።

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ኢንጂነር ዮናስ አያሌው በበኩላቸው፤ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለአጠቃላይ የሀገሪቱ እድገት የሚኖረው ሚና ትልቅ ነው። በዘርፉ የተሠማሩ አካላት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችል መድረክ መሆኑን ጠቅሰው ፤ በኤክስፖው አምራቾች የኮንስትራክሽንና ኢንጂነሪንግ ሙያ ላይ የሚሠሩ ተቋማት እንደሚሳተፉበትም ጠቁመዋል።

በመድረኩ በኢትዮጵያ የሚያመርቱና መሠረታዊ እቃዎችን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ ተቋማት እንደሚሳተፉ ገልጸው፤ አውደ ርዕይው በርካታ የውጭ ዜጎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ የሚያደርግ መሆኑን ገልጸዋል።

በባለፈው ዓመት ተመሳሳይ የኮንስትራክሽን አውደ ርዕይ የተካሄደ መሆኑንና ዘንድሮ ለሁለተኛ ጊዜ እንደሚካሄድ በመግለጽ ፣ አውደ ርዕዩ በከተማ መሠረተ ልማት ሚኒስቴርና በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን በጋራ የተዘጋጀ መሆኑም ተገልጿል።



# በምሥራቅ ጎጃም ዞን ወጣቶች የሀገር መከላከያ ሠራዊትን እየተቀላቀሉ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በምሥራቅ ጎጃም ዞን በ2016 ዓ.ም ሁለተኛው ዙር የሀገር መከላከያ ሠራዊት ምልመላ ሀገራቸውን በውትድርና ለማገልገል የፈለጉ የዞኑ ወጣቶችም ወደ ማሠልጠኛ ተቋማት እየተሸኙ ነው።

ወጣት መለሰ አሸናፊ የሀገር መከላከያ ሠራዊት አባላትን ከተቀላቀሉት ወጣቶች ውስጥ አንዱ ነው። አባቱ የሀገር መከላከያ ሠራዊትን በውትድርና እያገለገለ መሆኑን ገልጿል።

አባቱ ለሀገር እና ለሕዝብ እያገለገለ ስለመሆኑ የገለጸው ወጣት መለሰ ፤እሱም የአጎቱን እና የአክስቱን ልጆች ጨምሮ መመዝገቡን ገልጿል። "መከላከያን የተቀላቀልሁት የአባቶቻችንን አደራ ተቀብዬ ሀገሬን ለመጠበቅ ነው" ሲልም ተናግሯል ወጣቱ።

ምልምሎች የነገ ጀኔራሎች እንሆናለን ያሉት ወጣቶቹ መከላከያን በሙያቸውና በውትድርና ለማገልገል መነሳሳታቸውን ገልጸዋል።

የምሥራቅ ጎጃም ዞን ሰላምና ጸጥታ መምሪያ ኃላፊ አበባው በለጠ "የዞኑ ወጣቶች ሀገራቸውን ለመጠበቅ እያሳዩ ያሉት ሞራልና ስሜት የሚደነቅ ነው" ብለዋል።

በ2016 በጀት ዓመት ሁለተኛው ዙር የሀገር መከላከያ ሠራዊት ምልመላ በዞኑ ከሚገኙ 18 ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ወጣቶች በሙያቸውና በውትድርና ለማገልገል የሀገር መከላከያን እየተቀላቀሉ እንደሆነም ጠቁመዋል።

የምሥራቅ ጎጃም ዞን የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን መምሪያ መረጃ እንደሚያመለክተው ሠራዊቱን በሰው ኃይል ለማጠናከር የመመልመል እንዲሁም ወጣቱን የክብር ሙያ ባለቤት የማድረግ ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም መምሪያ ኃላፊው መናገራቸውን አሚኮ ዘግቧል።

# ሕገ-ወጥ የትምህርት ማስረጃ ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ እያሳደረ ነው

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ሕገ-ወጥ የትምህርት ማስረጃ የዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት በማሳጣትና በአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ላይ ችግር በመፍጠር በሀገር የኢኮኖሚ እድገት ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩን የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን አስታወቀ።

የባለሥልጣኑ የሕዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ ማርታ አድማሱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሕገ-ወጥ የትምህርት ማስረጃ የዜጎችን ብቃትና የተወዳዳሪነት አቅም በማሳጣት በተቋማት ላይ ብልሹ አሠራሮች እንዲሰፍንና በሀገር የኢኮኖሚ ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል።

ሕገወጥ የትምህርት ማስረጃ የብቃት መመዘኛና የመቁረጫ ነጥብ ያላሟሉ፤ ተዛማጅ ባልሆኑ የትምህርት ዘርፍና ፍቃድ በሌለው ኮሌጅ ማስረጃ የሚያገኙ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ የትክክለኛነት ማረጋገጫ ከተሠራላቸው 10 ሺህ 238 የትምህርት ማስረጃዎች አንድ ነጥብ 6 በመቶ ትክክለኛውን መስፈርት ማሟላታቸውን ገልጸዋል።

የትምህርት ማስረጃ የማጣራት ሥራው ለትምህርት ሚኒስቴርና የተጠሪ ተቋማት፣ የፌዴራልና የክልል መሥሪያ ቤት ሠራተኞችን እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸው፤ የማጣራት ስራ ሂደቱ ሲጠናቀቅ ውጤቱ ለሕዝብ ይፋ እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

ሕገ ወጥ የትምህርት ማስረጃ ብልሹ አሠራሮች እንዲፈጠሩ፣ እንዲበራከቱና የመልካም አስተዳደር ችግር ያስከትላል ያሉት ሥራ አስፈጻሚዋ፤ ዜጎችን የሥራ እድል መዝጋት፣ ለተገልጋዮች ቅሬታ መንስኤ በመሆንና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን በማሳጣት በተቋማት ላይ ያላቸውን እምነት እንዲያጡ ያደርጋል ብለዋል።

በአጠቃላይ ብቁና የተማረ ዜጋ ለማፍራት የሚወጣውን ከፍተኛ ወጪ ለብክነት እንደሚዳርግ ገልጸው፤ በተለይም በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ቀላል የማይባል ጉዳት ያደርሳል ሲሉ ተናግረዋል።

በተቋማት ላይ ማንኛውም ቅጥር ሲፈጸምና የደረጃ እድገት ሲሰጥ የትምህርተ ማስረጃ ማረጋገጥ ባህል እየሆነ መምጣቱን በመግለጽ፤ ተቋማት ሕገወጥ የትምህርት ማስረጃ በመያዝ በሚሠሩ ሠራተኞች መረጃቸው እንዲጣራ ማድረግና ርምጃ በመውሰድ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባም አመላክተዋል።

የዜጎች ክህሎትና የብቃት ማነስ ችግር በሀገር እድገት ላይ ከባድ ተጽዕኖ ማሳደሩን ገልጸው፤ ለዚህም የትምህርት ጥራት ማነስን እንደምክንያት የሚጠቀስ መሆኑን ገልጸዋል።

ትክክለኛ ያልሆነ ወይም ሕገ-ወጥ የትምህርት ማስረጃ በተበራከተ ቁጥር የሀገርን እድገት እንደሚፈታተን ጠቁመው፤ ችግሩን ለመቅረፍ የትምህርት ተቋማት የብቃትና የጥራት ማረጋገጫ እንዲኖራቸው እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

የዘርፉን ችግሮች ለመቅረፍ የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጥና የአቻ ግመታ መመሪያ ጸድቆ ከካቲት 20 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል መደረጉን አመልክተው፤ ችግሩን ለመቅረፍ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ሚና ሊወጡ እንደሚገባ አሳስበዋል።

# የውጭ ኢንቨስተሮች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ንግድ ከማመጣጠን ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅጾ እያበረከተ ይገኛል ብለዋል።

ኮሚሽኑ ከተቋቋመባቸው ዓላማዎች መካከል የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት መሳብ እንዲሁም በተያዘላቸው ጊዜ ወደ ሥራ እንዲሠማሩ ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው ያሉት ኮምሽነሯ፤ በተለይ የኢንቨስትመንት ከባቢ ሁኔታ ከመፍጠር አኳያ ሰፋፊ ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቁመዋል።

በሀገሪቱ የቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት አሁን ካለበት በበለጠ ለማሳደግ በውጭ ጉዳይ በኩል ከየሀገራቱ ከሚገኙ ኤምባሲዎች ጋር በትብብር እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ የቱርክና የማልታ ኢንቨስተሮችን ተጋብዘው በኢትዮጵያ ስላለው የኢንቨስትመንት አማራጭ ማስተዋወቅና ገለጻ መደረጉን ተናግረዋል።

በቀጣይም ሁለትና ሶስት የቢዝነስ ፎረሞችን ለማካሄድ የታቀዱ መኖራቸውንም አመላክተዋል።

እንደ ኮምሽነር ሃና ገለጻ፤ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ከመሳብ አኳያ ኢትዮጵያ ከምስራቅ አፍሪካ ቀዳሚ ናት። ነገር ግን ሀገሪቱ በየዘርፉ ካላት አቅም አኳያ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል።

በኢትዮጵያ ለኢንቨስትመንት በርካታ ምቹ ሁኔታዎች አሉ ያሉት ኮሚሽነር ሃና፤ ከዋና ዋናዎቹ መካከል ለመሠረተ ልማት ወጪ የሚደረግ ድጋፍ፣ የተለያዩ የኃይል አማራጮች፣ ከፍተኛ ጥሬ እቃና የምርት አስፈላጊ ግብዓት መኖር እንዲሁም ከፍተኛ የሰው ኃይል ተጠቃሽ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንትን ምቹ ለማድረግ የኢትዮጵያ መንግሥት ቋሚ የሆኑ የፖሊሲ ለውጦች እያደረገ እንደሚገኝ ኮምሽነር ሃና አስረድተዋል። ይህም ኢንቨስትመንትን ከማበረታታትና ኢኮኖሚውን ከመደገፍ አኳያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያሳድር ነው።

ለኢንቨስተሮች ፈቃድ ሲሰጥ ከሚፈጥሩት የሥራ እድል፣ ወጪና የገቢ ንግድ ለማመጣጠን ያላቸው ድርሻ፣ ከሚኖራቸው እውቀት፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ሽግግር አንጻር ነው ያሉት ኮሚሽነር ሃና፤ በዚህም ላይ ባለፉት ዓመታት ጥሩ የሆኑ ውጤቶች መመዝገባቸውን አስረድተዋል።

ኮሚሽነር ሃና፤ የተለያዩ ሀገራት ኢንቨስተሮች ለኢንቨስትመንት አማራጭ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ በመንግሥት ሴክተሮች ለኢንቨስትመንት ያሉ እድሎች በጥልቀት መረዳት የሚያስችሉ ሥራዎች ከማከናወን በተጨማሪ የግሉ ሴክተር የእውቀት፣ የልምድና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲያደርግ ቢዝነስ ፎረሞችን በማካሄድ በጋራ የሚወያዩበት መድረክ ተፈጥሯል ነው ያሉት።

በዚህም ኢትዮጵያ በግብርና፣ በማምረቻ፣ በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ፣ በቱሪዝም፣ በጤና እንዲሁም በሌሎችም ዘርፎች ላይ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው መዋዕለ ነዋያቸውን ለሚያፈሱ ባለሀብቶች የምትሰጠውን ማበረታቻ እያስተዋወቀች ትገኛለች ብለዋል።

በ2016 በጀት ዓመት ኮሚሽኑ 3 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ለመሳብ እቅድ ይዞ ሲሠራ መቆየቱን ጠቅሰው፤ በዚህም በበጀት ዓመቱ 10 ወራት 3 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት መሳብ ተችሏል ነው ያሉት።

ቻይና ፣ ኔዘርላንድ፣ ቱርክ እና ህንድ በኢትዮጵያ በውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ከሚሳተፉ ዋና ዋና ሀገራት መካከል መሆናቸውና የቻይና ኩባንያዎች ደግሞ ቀዳሚውን ደረጃ እንደሚይዙ ነው የጠቀሱት።

# የፕሪቶሪያው ስምምነት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትም ሥራ እንዲጀምሩ አስችሏል።

ይህ የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ለአፍሪካውያን ችግር አፍሪካውያም መፍትሄ ያስቀመጠ ስምምነት ተቃውሞና ስጋትም ገጥሞት ነበር። ስምምነቱንና አተገባበሩን አስመልክቶ ያነጋገርናቸው የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን ስምምነቱ እስካሁን ባስገኛቸው ጠቀሜታም ይሁን በቀጣይ በሚኖረው ፋይዳ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረከተ መሆኑን ይናገራሉ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት አቶ ሽመልስ ኃይሉ እንደሚያብራሩት፤ የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት መፈረም የንብረት ውድመትንና የሰው ልጅ ሕይወት የታደገ ነው። በጦርነቱ ሁለት ዓመታት በሰሜኑ ክፍል ልማትም ሆነ ሰላማዊ እንቅስቃሴ የሚታሰብ አልነበረም ይላሉ።

የነበረው ጥፋት በገንዘብ ብቻ የሚተመንም አልነበረም። ሰላማዊ ዜጎችም ስለሞቱባቸው ሰዎች ከማዘን ባለፈ የእነሱም ሞት ቅርብ እንደሆነ በማሰብ በከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ የከተተ ነው። በዚህ ስቃይ ውስጥ ለነበረ ሕዝብ ስምምነቱ ከቃላት በላይ የሆነ እፎይታ የሰጠ መሆኑን ያብራራሉ።

በተጨማሪ ስምምነቱ ፈጣንና ያልታሰበ ለኢትዮጵያም ለአፍሪካም እንደ ዓለምም ብዙ ትምህርት የሰጠ ሆኗል። በብዙ ሀገራት ተከስተው የነበኑ የእርስ በእርስ ግጭቶች ለመቆም ብዙ ልፋትና ረዘም ያለ ጊዜ የተሚጠይቁ ነበሩ። ምክንያቶቹ ደግሞ በቀላሉ መተማመን መፍጠር ስለማይቻልና ሌሎች የውጭ ኃይሎች የራሳቸውን ፍላጎትም ስለሚታከልበት ጭምር ነው። ከዚህ አኳያም ይህ ጦርነት በአጭር ጊዜ በስምምነት መቆሙ በራሱ ድል መሆኑን ይገልጻሉ።

አቶ ሽመልስ ገለጻ፤ ስምምነቱ ኢትዮጵያን ከተጨማሪ ረዥም ጦርነት የታደገ ብሎም ድብቅ አጀንዳ ይዘው የሚመጡ የውጭ ጣልቃ ገብነቶችን ያስቀረ ነው። ይህም እንደ ሀገር ብቻ ሳይሆን አፍሪካ በተለይም ግጭት ውስጥ ላሉ አርአያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። በሌላ በኩል ስምምነቱ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለሚታዩ ግጭቶች የመፍትሄ መንገድ አመላካች ነው።

ለኢትዮጵያ የእርስ በእርስ ግጭትና ጦርነት አንዱ የታሪክ አካል ነው። ነገር እንደ ሀገር ያለንን ንብረት ከማውደም እንደ ሕዝብ ወጣቶችን ከማስጨረስና ንጹሃንን ለስቃይ ከመዳረግ ባለፈ ምንም ያተረፍንበት ነገር የለም። ይህ አካሄድ በፖለቲካውም መስክ ይሄ ነው የሚባል ለውጥ ሳያመጣ እስካሁን ቆይቷል ነው ያሉት።

ይህም የመጪውን ትውልድ ተስፋ ከማቀጨጭ የዘለለ ፋይዳ አይኖረውም ። በመሆኑም የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ላለፈው ብቻ ሳይሆን ለቀጣዩም ጥሩ መልእክት የሚሰጥ ነው ያሉት።

በቅርቡ ብሔራዊ የደህንነት ምክር ቤት በሰጠው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ በፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት በአማራ፣ በአፋርና በትግራይ ክልሎች የመልሶ ግንባታ እና የመልሶ ማቋቋም ሥራዎች ተጀምረዋል። ሠብዓዊ ድጋፍም ያለመሰናከል ወደ ትግራይ መድረስ የሚችልበት ዕውድ ተፈጥሯለው። የሰላም ስምምነቱ በተፈረመ ማግሥት መንግሥት በሰላም ስምምነቱ ከገባው ግዴታ ያለፈ፣ መተማመን ለመፍጠር እና ሰላምን ለማጽናት አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን ርምጃዎች በተከታታይ ወስዷል።

በሰላም ስምምነቱ እስካሁን የተገኘው ውጤት እና እፎይታ እንደተጠበቀ ሆኖ ቀሪ ሥራዎችም አሉ። በተለይ በስምምነቱ መሠረት የሕወሓት ታጣቂዎች ትጥቅ መፍታት አለባቸው። የማንነት እና የአስተዳደር ወሰን ጥያቄ ያለባቸውን አካባቢዎች ጉዳይ እልባት ለመስጠት እንዲቻል የተቀመጠው አቅጣጫ ተግባራዊ መደረግ አለበት። በጦርነቱ የተፈናቀሉትን ለመመለስና ለማቋቋም የተጀመረው ሥራ እልባት ማግኘት እንዳለበት ብሔራዊ የደህንነት ምክር ቤት ገልጿል ።

መንግሥት የተቋረጡ መሠረተ ልማቶችን እና አገልግሎቶችን ለመጠገን እና መልሶ ለማስጀመር ወገቡን አሥሮ እየሠራ ነው። የፋይናንስ እና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን በትግራይ ክልል ለማሣለጥ እጅግ ከፍተኛ ወጪ አውጥቷል። የሰላም የትርፍ ድርሻው ታላቅ በመሆኑ መንግሥት ከሚጠበቅበትም አልፎ ቁስልን ለመሻር የሚያስችል ሥራ እየሠራ ነው ሲል ብሔራዊ የደህንነት ምክር ቤት የገለጸው።

የትግራይ ዲሞክራቲክ ፓርቲ ሊቀመንበር ዶክተር አረጋዊ በርሔ በበኩላቸው ስምምነቱ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሰላም ያመጣል ብሎ የጠበቀው ጉዳይ ስለነበር ለተግባራዊነቱም በመንግሥት በኩል ብዙ ተሠርቷል ። በዚህም የተወሰነ ርቀት መጓዝ ተችሏል ። እየተገኘ ያለውም ውጤት አሁን ካለው ጠቀሜታ ባለፈ ሌሎች ግጭቶችንም ለመፍታት እንደ ምሳሌ የሚጠቀስ ነው ይላሉ።

ስምምነቱ በእኛው በአፍሪካውያን መደረጉም የራሱ የሆነ ትልቅ ጥቅምና ትርጉም ያለው ነው። በወቅቱ ምእራባውያንና አሜሪካውያን ጣልቃ ለመግባት ብዙ ሞክረው ነበር፤ አሁንም እየሠሩ ያሉት ሥራ አለ ። ይሄ ለሕዝቡ የሚፈይደው ነገር አይኖርም። የውጭ ልቃገብነት ከሌለ ስምምነቱ ዘላቂ የመሆን እድሉ ሰፊ ነው። ለዚህም አፍሪካ አንድነት ያደረገው አስተዋጸኦ ይበል የሚያሰኝ እንደሆነ ያስረዳሉ።

አፍሪካ ህብረት ራሳችን ችለን እንድንጓዝ ብዙ ነገር ሠርቷል የሚሉት አረጋዊ (ዶ/ር) ፤ እስካሁን የተመዘገበው ውጤት ሊገኝ የቻለውም ለዚህ ነው ። የአሜሪካና የምእራባውያን ጣልቃ ገብነት ቢኖር ኖሮ አሁን የደረስንበትንም ውጤት ማየት አንችልም ነበር። ይህም ሆኖ በስምምነቱ ተኩስ ቆሞ ከፊል ውጤት ቢገኝበትም ከሚጠበቀው አኳያ ግን በቂ እንዳልሆነ ይናገራሉ።

ለስምምነቱ እንደ ዋና ጉዳይ ሊወሰድ የሚገባውና ሰላም ለማስፈን መሠረት የሆነው አንቀጽ አስር ላይ የሰፈረው ጉዳይ እስካሁን በቂ ትኩረት አላገኘም። በዚህ አንቀጽ ላይ የሰፈረው ስምምነት በትግራይ አካታች የሆነ ጊዜያዊ አስተዳደር እንዲመሠረት የሚያዝ ነው ይላሉ ።

አካታች ማለት ደግሞ ሌሎች ፖለቲካዊና ማህበራዊ ቡድኖችን ያቀፈ ማለት ነው ። የእነዚህ አካላት ቢካተቱ የሰላም ስምምነቱን እውን ለማድረግ ትልቅ እድል የሚከፍት ነው። ይህ ቢተገበር የተጀመሩት ትጥቅ የማስፈታት ፣ ሠራዊቱን በተለያየ ቦታ የማስፈር ፣ የርዳታ ተደራሽነትን የማረጋገጥ ሥራ ሁሉ ውጤታማ ይሆን ነበር የሚል ሃሳብ አላቸው።

ነገር ግን ሥልጣኑን ህወሓት ጠቅልሎ ጊዜያዊ አስተዳደር እንዲሆን ተደረገ። ህወሓት ደግሞ ለውድቀት ያበቁትን ፖሊሲዎች እስካሁንም እየተከተለ ይገኛል። በመሆኑም ወደ ኋላ ተመልሶ በስምምነቱ መሠረት ይህንን ማስተካከል ይጠበቃል። ካልሆነ ግን የስምምነቱ ውጤታማነት ጥያቄ ውስጥ ሊገባ ይችላል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

# 89 ሺህ ተፈናቃዮች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በመውሰድ ከ123ሺ ተፈናቃዮች ውስጥ 89ሺ ተፈናቃዮቹን ወደ ቀያቸው መመለስ ተችሏል።

የቀሩትን ተፈናቃዮች ወደቀያቸው የመመለሱ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመው፤ አሁን ላይ የዞኑ ሰላም እየተሻሻለ መምጣቱን ገልጸዋል።

ባለፉት ሁለት እና ሶስት ዓመታት ጽንፈኞች ዘግናኝ ድርጊቶች ሲፈጽሙ ነበር ያሉት አቶ መሬሳ፤ ዝርፊያ፣ ሴቶችን መድፈር፣ እንዲሁም ግድያ በመፈጸም የዞኑን ሰላም ሲያውኩ መቆየታቸውን ተናግረዋል።

በዞኑ ያጋጠመውን የሰላም ችግር ለመቅረፍ ባለፉት አራት ወራት ውስጥ በጽንፈኞች ላይ በተወሰደው የተቀናጀ ርምጃ አብዛኞዎቹ መደምሰሳቸውን ተናግረው፤ 628 የሚሆኑት ለጸጥታ አስከባሪዎች እጃቸውን ሰጥተው ሥልጠና እየወሰዱ ወደ ማህበረሰቡ እየተቀላቀሉ መሆኑን ገልጸዋል።

በዞኑ ሰላም ከማስጠበቅ ሥራ ጎን ለጎን የልማት ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን የተናገሩት አቶ መሬሳ፤ አሁን ላይ በተገኘው ሰላም መደበኛ የግብርና እና የትምህርት የልማት ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን አመላክተዋል።

በዞኑ የበጋ ስንዴ እና የበልግ ልማት ሥራዎች መከናወናቸውን ተናግረው ፤ ለመኸር ወቅት የእርሻ ሥራም ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል። ከተፈቀደው 206 ሺ ኩንታል ማዳበሪያ 160ሺ ኩንታል ለአርሶ አደሩ መሠራጨቱን ጠቁመዋል።

በአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር 179 ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል መታቀዱን የገለጹት የዞኑ አስተዳዳሪ ፤ይህንን ለማሳካት 48 ነጥብ 3 ሄክታር መሬት ለማዘጋጀት ከታቀደው ውስጥ 28ሺ ሄክታር መሬት መዘጋጀቱን አመላክተዋል።

በትምህርቱም ዘርፍ ካሉ ችግሮች ለመላቀቅ ከተማሪዎች፣ ወላጆች እና መምህራን ጋር ሰፊ ውይይት ተደርጓል። የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል የማጠናከሪያ ትምህርት እየተሰጠ መሆኑን ተናግረው፤ በዓመቱ የተማሪዎችን ውጤት 20 በመቶ ለማሻሻል አቅጣጫ ተቀምጦ እየተሠራበት መሆኑንም ተናግረዋል።

ባለፉት ሶስት ዓመታት መንግሥት መሠረተ ልማቶችን ለማሟላት ሰባት ቢሊዮን ብር ቢመድብም በጽንፈኞች ድርጊት መስተጓጎሉን ገልጸው፤ በአሁኑ ጊዜ ሁሉንም ወደ ግንባታ የማስገባት ሥራዎች እየተሠሩ ነው ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አጀንዳ የማሰባሰብ ተግባሩ ውጤታማ እንዲሆን ሁሉም የድርሻውን ይወጣ!

በ2017 ዓ.ም በሀገራችን እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሀገራዊ መግባባት ተፈጥሮ ማየትን ራዕዩ አድርጎ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን በታሪክ ሂደት የተፈጠሩ አለመግባባቶችን በማያዳግም መልኩ እልባት ለመስጠት ዘርፈ ብዙ ጥረቶችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ኮሚሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ልዩነታቸውን ወደ ጎን በማድረግ በሰላማዊ አማራጭ ብቻ ሀገራቸውን እንዲያሸጋግሩ ጥሪ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በሁለት ዓመት ተኩል ቆይታውም የተለያዩ ዓለም አቀፍ ልምዶችን ከመቀመር ባሻገር የታችኛው የኅብረተሰብ ክፍል ድረስ በመውረድ ስለምክክር አስፈላጊነት ሰፋ ያሉ ግንዛቤዎችን ሲፈጥር ቆይቷል፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎንም በአስር ክልሎች የተሳታፊና የተባባሪ አካላት ምርጫ አካሂዷል፤ ሥልጠናም ሰጥቷል፡፡ እነዚህ ሥራዎች በተጠናቀቁባቸው ክልሎች ደግሞ አጀንዳ የመቅረጽ እና በተቀረጹት አጀንዳዎች ላይም ምክክር አድርጎ የመቋጨት ሥራ ይሠራል፡፡

ከግንቦት 21 ጀምሮ እስከ 27 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ባሉት ቀናትም አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ላይ የአጀንዳ ማሰባሰብ ተግባር ያከናውናል፡፡ የምክክር አጀንዳዎችን ማሰባሰብ፣ ልየታ እና ቀረጻ በሀገራዊ ምክክር ሂደት ወሳኝ ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ይህ ሂደት ደግሞ በርካታ ልምዶች የሚቀመሩበት ለሰላምና እርቅ የተመረጠው ዘዴ ትክክል መሆን አለመሆኑ የሚታይበትና የሚቃኝበት ነው፡፡

በኢትዮጵያ በሂደት ላይ ያለው ምክክር አጀንዳዎቹ አስቀድመው የተወሰኑ ባይሆኑም መርሆዎች ግን ተቀምጠውለታል፡፡ ምክክር እንዲካሄድባቸው የሚቀረጹ አጀንዳዎች እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ማተኮር እንዳለባቸው፣ የአለመግባባት መንስዔዎችን በትክክል በሚዳስሱ አጀንዳዎች ላይ የሚያተኩሩ እና ጥልቀትና አግባብነት ያላቸው መሆን እንዳለባቸው መርሆዎች መቀመጣቸውን የብሔራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ሲገልጽ ቆይቷል፡፡ በአዲስ አበባም የሚካሄደው አጀንዳዎችን የማሰባሰብ ሂደት በተቀመጡለት መርሆዎች መሠረት እንደሚከናወንም ተጠቁሟል፡፡

አዲስ አበባ አንጻራዊ ሰላም ያለባትና ለብሔራዊ ምክክርም የተሻለ መደላድል የተፈጠረባት ከተማ በመሆኗ የአጀንዳ ማሰባሰቡ ተግባር የተሳካ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ በከተማዋ ሃሳብ አለኝ የሚል የኅብረተሰብ ክፍል ተወካዮች ሃሳባቸውን ያለምን ገደብ የሚሰጡበትና በመደማመጥ ጉዳዮች እልባት የሚያገኙበት ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ይህን መነሻ በማድረግም ወደሌሎች ክልልች ተሞክሮውን የማስፋት ሥራም በቀጣይነት የሚከናወን ይሆናል፡፡ በቀጣይም የምክክሩን አጀንዳዎችን ከኅብረተሰቡ የመቀበልና ምክክሩን ወደ መሬት የማውረድ ሥራዎች ይከናወናሉ፡ በአጠቃላይ ከአዲስ አበባ የሚገኘው ልምድ በቀጣይ ለሚካሄዱ የአጀንዳ ማሰባሰብ ሥራዎች እርሾ ሆኖ ያገለግላል፡፡

በተለይም ሰላም በሰፈነባቸው አካባቢዎች ከአዲስ አበባ ልምድ በመቅሰም በተቻለ ፍጥነት ወደ አጀንዳ ማሰባሰቡ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡ የጸጥታ ችግር ያለባቸው አካባቢዎችም ቢሆኑ ከሞላ ጎደል መንግሥትም ጣልቃ ገብቶ በአካባቢው ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁም ችግሩን እንፈታለን ብለው የተነሱትም ኃይሎችም ችግራቸውን በውይይት ለመፍታት መሞከር አለባቸው፡፡

ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ግጭት፤ ጦርነትና መወነጃጀል ሳይሆን ውይይትና ምክክር ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም ችግሮችን በውይይት የመፍታት ባህልም እንደሀገር ከማዳበር ውጪ ፍላጎትን በኃይል መጫን ጊዜ ያለፈበት ተግባር ነው፡፡ ስለዚህም ግጭትንና ጦርነትን እንደ ችገር መፍቻ የወሰዱ አካላት የሕዝባቸውንና ሀገራቸውን መጻኢ ጊዜ ማሳመር ከፈለጉ የተፈጠረውን የምክክር ዕድል ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡

በምክክር የመግባባት ሂደት በየምዕራፉ መመካከርንና መግባባትን ይጠይቃል፡፡ በዚሁም መሠረት ምክክር በሚካሄድባቸው አጀንዳዎች ላይ መመካከሩና መግባባት ላይ መድረሱ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነት መሠረት በማድረግ አጀንዳዎችን ከምክክር ሂደቱ ተሳታፊዎች፣ ከተለያዩ ጥናቶች፣ ግለሰቦች ወይም ተቋማት ከሚሰጧቸው የአጀንዳ ሃሳቦች በማሰባሰብ የመለየት፣ የመቅረጽ እንዲሁም ቅደም ተከተል በማስያዝ ምክክር እንዲደረግባቸው ያደርጋል፡፡

አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ የምክክር ኮሚሽኑ በበርካታ ተግዳሮቶች ውስጥ ሆኖ ውጤት እያስመዘገበ ነው፡፡ በሂደቱም ወሳኝ የሚባለውን የአጀንዳ ማሰባበሰብ ሥራ ለማከናወን ዝግጅቱን አጠናቋል፡፡

ስለዚህም ነገ በአዲስ አበባ የሚጀመረው አጀንዳ የማሰባሰቡ ሥራ ውጤታማ እንዲሆንና የተሻለ ተሞክሮ ሆኖ ወደ ሌሎች ክልሎችም እንዲሸጋገር የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ኃላፊነታቸውን በሚገባ ሊወጡ ይገባል፡፡


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ‹‹ኢትዮጵያ እንደምን ሠለጠነች?››

ሚሊዮን ሺበሺ

የታሪክ መታጠፊያዎች በግለሰቦች የሚጀመሩ ናቸው፡፡ ዘመን ተሻጋሪ ቅርሶች ሺህ ዘመናትን የሚመሰክሩት በግለሰቦች ታስበው፣ በብዙዎች ተፈጽመው ነው፡፡ እነዚህ ዘመን ተሻጋሪ ሥራዎች የአንዲት ሀገር የሥልጣኔ መለያ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፤ የአክሱም ዘመነ መንግሥት እያልን እንጠራለን፤ የአክሱም ዘመን የሥልጣኔ ምልክት ነው፡፡ ምክንያቱም የአክሱም ሐውልት ቆሞ እየመሰከረ ነው፡፡ የላሊበላ አንድ ወጥ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት እና የፋሲል ግንብ የዘመናት ምስክሮች ናቸው፡፡ በዓለም አቀፉ የሚዲያ ተቋም ቢቢሲ የሀገሮች ታሪክ ላይ ኢትዮጵያ በእነዚህ ዘመን ተሻጋሪ ሥራዎች ትጠቀሳለች፡፡

በእንዲህ አይነት ሥልጣኔዎች የምትታወቀው ኢትዮጵያ ከመካከለኛው ዘመን በኋላ የፖለቲካ ውጥረቶች የበዙባት ሆናለች፡፡ ይባስ ብሎ ደግሞ ከ1966 ዓ.ም በኋላ በተፈጠረው አብዮት የውስጥ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ተባብሰው በዓይን የሚታዩ ነገሮች እንዳይኖሩ አድርጓል፡፡ በዓይን የሚታዩ ማራኪ ነገሮች ከመሥራት ይልቅ የፖለቲካ ግርግሮችና የውስጥ ጦርነቶች የበለጠ ቦታ ያዙ፡፡ በዚህም ምክንያት አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የራሱን ሀገር የሚራገም ሆነ፡፡ ባለፈበት ቦታ ሁሉ ንፁህ አካባቢ ስለማያገኝ ‹‹አይ! ኢትዮጵያ!›› እያለ ሀገሩን ያማርራል፡፡ ልክ የሌላ ሀገር ዜጋ የሆነ ይመስል አካባቢው አምሮና ተውቦ ማየት የሚፈልገው ሌሎች በሚሠሩት ነው፡፡

ይህ ችግር ላለፉት ብዙ ዓመታት ሲንከባለል ቆይቷል፡፡ አሁን ግን ባለራዕይ፣ አርቆ አስተዋይ እና ሥልጣኔ የገባቸው መሪዎችን አግኝቷል፡፡ በውጭ ሀገር ያዩትን ሥልጣኔ ‹‹እገሌ ሀገር የሠለጠነችው እንዲህ ነው...›› እያሉ ተረት ከመናገር ይልቅ ራስን እንዴት ማሠልጠን እንደሚቻል እያሳዩን ነው፡፡ ቀጣዩ ትውልድ ‹‹ኢትዮጵያ እንደምን ሠለጠነች?›› ብሎ የሚጠይቅ ይሆናል፡፡

የአራት ኪሎና አካባቢዋ የኮሪደር ልማት ከተጀመረ ገና ሦስት ወር እንኳን አልሞላውም፡፡ አሁን በዚያ አካባቢ የሚያልፉ ሰዎች ‹‹ሌላ ሀገር ያለሁ መሰለኝ!›› ሲባባሉ የሰማሁት በጆሮዬ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች በቴሌቭዥንና በፊልም የሚያዩትን ወይም አውሮፓና አሜሪካ ሄደው የመጡ ሰዎች ሲያወሩ የሰሙትን ወይም ራሳቸው ሄደው ያዩትን የሠለጠነ ሀገር ማራኪ ነገር ማየት ቻሉ ማለት ነው፡፡ ሌሎች አካባቢዎችንም እንደዚህ ማድረግ እንደሚቻል ሰርቶ ማሳያ (ሞዴል) አገኙ ማለት ነው፡፡ ኢትዮጵያን የሠለጠኑ ናቸው እንደሚባሉት አውሮፓና አሜሪካ ማድረግ እንደሚቻል አረጋገጡ ማለት ነው፡፡

አንድ ግን ግርም የሚለኝ ነገር አለ፡፡ መንግሥትን እንቃወማለን የሚሉ አካላት አሥር ጊዜ ምሳሌ የሚጠቅሱት የሠለጠኑ ሀገራትን የአካባቢ አያያዝ ነው፡፡ የአውሮፓና አሜሪካ ሀገራትን እየጠቀሱ ንጽህናቸውን ይናገራሉ፡፡ አዲስ አበባን ‹‹የገማች ናት፣ የቆሸሸች ናት፣ በዚህ መንግሥት እየተመራች....›› ይላሉ፡፡ እንዲህ ሲሠራ ግን አያመሰግኑም፡፡ ጭራሽ ይባስ ብሎ መሠራቱን የሚቃወሙም አሉ፡፡ እነዚህ አካላት ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ ከሀገር ዳር ድንበርና ከውጭ ጉዳይ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ አስተያየት ቢሰጡ ጥሩ ነበር፤ ሀገር ውስጥ የሚሠራ፣ ጥቅም ብቻ እንጂ ምንም ጉዳት የሌለውን ነገር ከተቃወሙ የምርም የመቃወም ሱስ ብቻ ነው፡፡ ደግነቱ መንግሥት እንዲህ አይነቶችን ባለመስማት አዲስ አበባን የሥልጥንና ተምሳሌት እያደረጋት ነው፡፡

> **ከዚህ በኋላ ‹‹ኢትዮጵያ እንደምን ሠለጠነች?›› የሚል ትርክት ይፈጠራል፡፡ ከምን አይነት ኋላቀር አኗኗር ወደ እንዲህ አይነት የሠለጠነ አኗኗር እንደተቀየረች ታሪክ ይናገራል**

ከዚህ በኋላ ‹‹ኢትዮጵያ እንደምን ሠለጠነች?›› የሚል ትርክት ይፈጠራል፡፡ ከምን አይነት ኋላቀር አኗኗር ወደ እንዲህ አይነት የሠለጠነ አኗኗር እንደተቀየረች ታሪክ ይናገራል፡፡ ‹‹እነሆ በዚያን ጊዜ እገሌ የሚባል መሪ ነበር፣ እገሌ የምትባል የአዲስ አበባ ከንቲባ ነበረች...›› እየተባለ ይነገራል፡፡ በእነዚህ የሠለጠኑ መሪዎች አፍላቂነትና አስፈፃሚነት ይህ ትውልድ የዚህ ሥልጡን ዐሻራ ባለቤት ይሆናል ማለት ነው፡፡

ይህ እውን ይሆን ዘንድ ግን ሁሉም ተባባሪ ሊሆን ይገባል፡፡ ሀገር የሚገነባው በጥቂቶች አሳቢነት ቢሆንም የሚሳካው ግን የሁሉም ትብብር ሲኖርበት ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ እገዛዎች ብዙ አይነት ናቸው፡፡ ለምሳሌ፤ ጽዱ ኢትዮጵያ ለመፍጠር ባለፉት ሳምንታት የገንዘብ መዋጮ ዘመቻ ነበር፡፡ በዚህ ታሪካዊ ሂደት ውስጥ በ100 ብር እንኳን ዐሻራን ማስመቀጥ ይቻላል ማለት ነው፡፡ ሀገርን በመገንባት ሂደት ውስጥ እንደመሳተፍ ታሪካዊ ዕድል የለም፡፡

ሌላው እና ዋናው እገዛ ግን የሃሳብ ሞራል መስጠት ነው፡፡ ማድነቅን ልማድ ማድረግ ነው፡፡ ሥራዎች እስከሚጠናቀቁ ድረስ ብዙ አስቸጋሪ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ መንገዶች ይዘጋጋሉ፣ አቧራ እና ጭቃ በጣም ሊያስቸግር ይችላል፤ ብዙ ቦታ መንገዶች ስለሚዘጉ ረዘም ላሉ ደቂቃዎች በእግር መሄድ ያጋጥማል፣ በመንገዶች መዘጋት ምክንያት ትራንስፖርት ላይኖር ይችላል... የመሳሰሉት ችግሮች ያጋጥማሉ፡፡ እነዚህ ችግሮች ሲያጋጥሙ ከማማረር ይልቅ በአርቆ አስተዋይነት የነገውን ማሰብ ብልህነት ይሆናል፡፡ ለምሳሌ፤ አራት ኪሎ ከዛሬ ሁለት ወር በፊት እና ዛሬ ሌላ ሀገር እና ሌላ ሀገር እንደማለት ነው፡፡ ከዛሬ ሁለት ወር በፊት አካባቢው ሁሉ ተቆፍሮ ተቆፍሮ መሻገሪያ እስከሚያስቸግር ድረስ ችግር ነበር፣ በአካባቢው ውሃ እና መብራት እየተቋረጠ ለቀናት ችግሮች ነበሩ፡፡ የዛሬዋ አራት ኪሎ ግን የራስን ሀገር በቅናት እና በስስት ለማየት የምታስገድድ ናት፡፡ ዝናብ ሲዘንብ መንገደኛ የሚተላለፈው ቆሞ ወረፋ እየተጠባበቀ ነበር፡፡ መቆሙ ብቻ አልነበረም ችግሩ፤ በአስፋልት ላይ የሚያልፍ መኪና ውሃ ረጭቶበት ይሄዳል፤ ምክንያቱም አስፋልቱ ውሃ የሚያጠራቅም ነበር፡፡ አሁን ግን የእግረኛ መንገዱ ከመኪና ወርዶ በእግር ለመሄድ የሚያስመኝ ነው፡፡ አሁን ግን የሚተላለፉ ሰዎች እንኳን ወረፋ ሊጠባበቁ ላይተያዩ ሁሉ ይችላሉ፡፡ አስፋልቱ እንኳን ውሃ ሊያጠራቅም ዝናብ መዝነቡ የሚታየው ከሰማይ ሲወርድ ብቻ ነው፡፡ ሁለት ወር እነዚያን ችግሮች የተቋቋመ የአራት ኪሎና አካባቢዋ ነዋሪ አሁን ሌሎች አካባቢዎችን የሚያስቀና ሆነ ማለት ነው፡፡

አራት ኪሎና አካባቢዋ ውብ መሆኗ አዲስ አበባ ውብ ሆነች ማለት ነው ወይ? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፤ መልሱ ግን አራት ኪሎና ፒያሳ ብቻ ሳይሆን ሌሎች የአዲስ አበባ አካባቢዎችም እየተሠሩ ነው፡፡ በሂደት ሁሉም ይሠራሉ ማለት ነው፡፡ አዲስ አበባ ሥልጡን እና ውብ ሆነች ማለት ኢትዮጵያ ሠለጠነች ማለት ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ቢነሳ በጣም ተገቢ ጥያቄ ነው፡፡ ሁለት ነገር ግን ልብ እንበል፡፡ አንደኛ፤ የዓለም መሪዎችና ዲፕሎማት ኢትዮጵያን የሚያውቋት መጀመሪያ በአዲስ አበባ ነው፡፡ የሠለጠኑ የዓለም ሀገራትን በዋናነት የምናውቃቸው በዋና ከተሞቻቸው ነው፡፡ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ ስለሆነችና የሁሉም ኢትዮጵያውያን መኖሪያ ስለሆነች ዋናዋ ኢትዮጵያ ናት ማለት ነው፡፡

ሁለተኛውና ዋናው ምክንያት ግን፤ ሁሉንም የኢትዮጵያ አካባቢዎች እንደ አዲስ አበባ ለማድረግ አርዓያ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ አዲስ አበባ ላይ ብቻ ሆነ እያሉ ከማማረር ሌሎች አካባቢዎችም እንደ አዲስ አበባ እንዲሆኑ መረባረብ ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡ ይህ ትውልድ ይህን ሥራ ከሠራ ‹‹ኢትዮጵያ እንደምን ሰለጠነች?›› የሚል ትርክት አካል ይሆናል፡፡

# ተጠየቅ

# “ባለሥልጣኑ - በዓለም አቀፍ ደረጃ ድርሻውን መወጣት የሚያስችለው አደረጃጀት ቢፈጠርለት ጥሩ ነው”

- አቶ አስራት መኩሪያ

የደቡብ ምዕራብ ሕዝቦች ክልል የቡና ሻይ ቢሮ ኃላፊ፤

መክሊት ወንድወሰን፣ ሞገስ ተስፋ እና ሙሉቀን ታደገ

**የደቡብ ምዕራብ ሕዝቦች ክልል ገበያ ተኮር በሆኑ ምርቶችን በማምረት ይታወቃል:: እነዚህ ምርቶች ደግሞ ለሀገራችን ከፍተኛ ገንዘብ የሚያስገኙ፣ ለወጪ ንግዱም ከፍ ያለ አበርክቶ ያላቸው ናቸው:: በዚህም እንደ ቡናና ሻይ ያሉ ከፍ ያለ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸውን ምርቶች በምርት፣ በግብይት ሥርዓቱም የተሻለ ነገርን ለመፍጠር ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራባቸው ይገኛል::**

**ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዘርፉ የሚስተዋሉ ክፍተቶች የቅሬታ ምንጭ እየሆኑ፤ የግብይት ሥርዓቱንም እየፈተኑ ይገኛል:: በዚህ ረገድ በተለይም በቡና ግብይት ሥርዓቱ ላይ በተፈጠረ አሰራር አምራቾች እና ነጋዴዎች ከፍተኛ ችግር እንዳጋጠማቸው ይናገራሉ:: ይሄ ችግር ከሚታይባቸው አካባቢዎች መካከል የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል አንዱ ሲሆን፤ እኛም ለዛሬው የተጠየቅ ዓምዳችን ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የደቡብ ምዕራብ ሕዝቦች ክልል የቡና ሻይ ቢሮ ኃላፊ አቶ አስራት መኩሪያን ጠይቀን ያገኘነውን ምላሽ እንደሚከተለው አቅርበነዋል:: መልካም ንባብ::**



**አዲስ ዘመን፡- ቢሮአችሁ የተሰጠውን ኃላፊነት ከመወጣት አኳያ በዘርፉ ክልሉ ያለውን አቅም ምን ያህል አውቆ ነው ወደሥራ የገባው?**

**አቶ አስራት፡-** የደቡብ ምዕራብ ሕዝቦች ክልል በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ገበያ ተወዳዳሪ የሆኑና የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙ ሰብሎችን፤ በተለይም ቡና እና በቅመማ ቅመም እንዲሁም የሻይ ቅጠልን የመሰሉ የግብርና ምርቶችን በማምረት ይታወቃል::

የቡና ምርትን በተመለከት ክልሉ በሽፋንም ሆነ በአቅርቦት ከኦሮሚያ ክልል ቀጥሎ ከፍተኛ ድርሻ ያለው ሲሆን፤ ከ560 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በቡና ማሳ መሸፈን የቻለ ነው:: ከዚህ ባሻገር በክልሉ ከ513 ሺህ በላይ ቡና አምራች አርሶአደሮች ያሉ ሲሆን፤ ቡናን በአራት አይነት የአመራረት ዘዴዎች (ከጫካ፣ ከፊል ጫካ፣ በዘመናዊ የተከላና እና ከጓሮ) ያመርታሉ::

ከቅመማ ቅመም ምርት ጋር በተያያዘ በክልሉ ከ80 ሺህ ሄክታር በላይ ዓመታዊ እና ‹‹ሰንባች›› ቅመማ ቅመሞች ይለማሉ:: በተጨማሪም በሻይ እርሻ በክልላችን ኢስት አፍሪካ እና ኢትዮ አግሮሴፍ ውሸውሽ በተባሉ ሁለት ትላልቅ ኩባንያዎች እንዲሁም በኮንትራክት የታቀፉ አርሶ አደሮች ከ2ሺህ 282 ሄክታር በላይ ማሳ እየለማ ነው:: ከዚህ ውስጥ 446 ሄክታሩ በኮንትራክት እርሻ በታቀፉ አርሶ አደሮች የለማ ነው:: በዚህም 512 የሚሆኑ አርሶ አደሮችን በህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጀት ተችሏል::

**አዲስ ዘመን፡- ቢሮው በ2016 ዓመት በጀት ዓመት ምን አቅዶ ምን አከናወነ? ከእቅድ አንጻር አፈጻጸማችሁ ምን ይመስላል?**

**አቶ አስራት፡-** በክልሉ ያለውን አቅም፣ እንዲሁም የ2015 በጀት ዓመት አፈጻጸማችንን ማዕከል በማድረግ ነው ለ2016 በጀት ዓመት እቅድ ያስቀመጥነው:: በዚህም በ2015 በጀት ዓመት የነበሩን ጥንካሬዎች እና ጉድለቶች በመገምገም በ2016 በጀት ዓመት ምርታማነትን ማሻሻል፤ እንዲሁም የምርት ዝግጅትና አቅርቦት ላይ ያለ የግብይት ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ ሥራዎችን አቅደን ሰርተናል::

በአመቱ አጠቃላይ ከሰራናቸው ስራዎች መካከል የቡና ማሳን ማስፋት እና የቡና ምርጥ ዘር ማዘጋጀት የሚሉት በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሾች ናቸው:: ከዚህ አኳያ 54 ሺህ አንድ መቶ ኪሎ ግራም የቡና ምርጥ ዘር እናዘጋጃለን ብለን አቅደን፤ ከእቅድ በላይ ከ59 ሺህ ኪሎ ግራም በላይ የቡና ምርጥ ዘር ማዘጋጀት ችለናል::

የምናዘጋጀው ምርጥ ዘር ለእኛ ክልል ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ሦስት ክልሎችም የሚሰራጭ ነው:: 16 ሺህ ኪሎ ግራም የሚሆን የቡና ምርጥ ዘር በሲዳማ፣ ማዕከላዊና ደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች ተሰራጭቷል:: ከክልሎች በተጨማሪም ቦንጋ፤ ዋቻሞ እና ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲዎች ምርጥ ዘር ወስደዋል:: በነገራችን ላይ ይህን ምርጥ ዘር ከቢሮው በተጨማሪ የብቃት ማረጋገጫ ‹‹ሲኦሲ›› ያላቸው አርሶአደሮች ጭምር ያመረታሉ::

እነዚህ አርሶአደሮች በከፋ ዞን በአራት ህብረት ሥራ ማህበራት የተደራጁና ‹‹በኳራንታይን›› ማእከል ወይም በእጽዋት ዘር ጥራት ማዕከል የብቃት ማረጋገጫ ‹‹ሲኦሲ›› የተሰጣቸው ናቸው:: አርሶ አደሮቹ በየአመቱ ስልጠና ይሰጣቸዋል::

በዚህ ዓመት ሶስቱም ዩኒቨርሲቲዎች ከእኛ ምርጥ ዘር ወስደዋል:: እነዚህን ጨምሮ በእኛ ክልልም ልማቱ ባልተስፋፋባቸው አካባቢዎች በፕሮጀክቶች እና በተለያዩ ድጋፎች በዞኖች እና በወረዳዎችም ዘር የማሰራጨት ሥራዎች እየተሰሩ ነው:: ከዚህ አኳያ በክልሉ የቡና ዘር በሁለት ወቅት ነው የሚፈሰው:: የመጀመሪያው ዙር ከመስከረም እስከ ህዳር ሲሆን፤ ሁለተኛው ዙር ደግሞ ከሚያዝያ ጀምሮ ክረምቱን የሚፈስ ነው:: በመጀመሪያው ዙር ወደ 13 ሺህ ኪሎ ግራም ምርጥ ዘር ቡና በክልሉ ለማፍሰስ አቅደን በዘጠኝ ወር ውስጥ 11 ሺህ ኪሎ ግራም የሚሆን ማፍሰስ ችለናል::

በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ ከበልግ ተከላ ጀምሮ እና በክረምቱን 72 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን በተለያየ ደረጃ የሚገኝን የቡና ችግኝ ለመትከል አቅደን በዘጠኝ ወር ውስጥ 71 ሚሊዮን የሚጠጋ የቡና ችግኝ ለተከላ ተለይቷል:: ከሚያዝያ ወር ጀምሮ ተከላውም ተጀምሯል:: እስከ ሰኔ 30 ድረስም 42 ሚሊዮን የቡና ችግኝ ይተከላል:: ለዚህ ይረዳ ዘንድ 31 ሚሊዮን የሚሆን የቡና መትከያ ጉድጓድም ተዘጋጅቷል::

በቅመማ ቅመም ከእቅድ በላይ ተከላ ማካሄድ ችለናል:: በበጀት አመቱ 38 ሄክታር አመታዊና ሰንባች ቅመማ ቅመም አይነቶች ተከላ ለማካሄድ፤ እስከ ዘጠኝ ወር ደግሞ 24 ሺህ በላይ ችግኝ ተከላ እናከናውናለን ብለን አቅድን 25 ሺህ ችግኝ በመትከል ከእቅድ በላይ ማሳካት ችለናል::

በሻይ 35 ሄክታር በአርሶ አደሩ እናለማለን ተብሎ ታቅዶ በዘጠኝ ወር ውስጥ 10 ሄክታር ማልማት ተችሏል:: የሻይ ግብርና ሥራ በዋናነት በክረምት ስለሚከናወን እቅዱን ለማሳካት ክረምት ላይ ቀሪ ስራዎች ይከናወናሉ:: በኮንትራክት ፋርሚንግ ደግሞ 10 ሄክታር ለማልማት ታቅዶ 12 ሄክታር ሻይ ማልማት ተችሏል::

የቡና ምርቱን ለማሳደግ ያረጀና ምርት ያቆመ የቡና ግንድ በጉንደላ እና በነቀላ ማደስ ያፈልጋል:: ከዚህ አኳያ 4ሺ ሄክታር በላይ እናድሳለን ብለን አቅደን ነበር:: በዘጠኝ ወራት ብቻ የእቅዳችንን 77 በመቶ ወይም ሦስት ሺህ 600 ሄክታር የቡና እደሳ ስራዎችን ሰርተናል::

እንደሚታወቀው ቡና፣ ሻይ እና ቅመማ ቅመም በእጅጉ ስትራቴጂክ ምርቶች ናቸው:: እነዚህ የግብርና ምርቶች እንደሌሎች ምርቶች ለቤት ፍጆታ በማዋል መጨረስ ስለማይቻል ወደ ገበያ የሚወጡ ናቸው:: ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ናቸው:: በተለይም ለውጭ ገበያ ሲቀርቡ የውጭ ምንዛሬን የሚያስገኙ ናቸው:: ከዚህ አንጻር በበጀት አመቱ ወደ 67 ሺህ 348 ቶን የታጠበና ያልታጠበ ቡና ለማዕከላዊ ገበያ እናቀርባለን ብለን አቅደን ነበር:: ከዚህ አንጻር በዘጠኝ ወራት ውስጥ 38 ሺህ 40 ወይም 87 በመቶ ማሳካት ችለናል::

በቅመማ ቅመም ዘርፍ በበጀት ዓመቱ 54 ሺህ ቶን ቡና ለማዕከላዊ ገበያ እናቀርባለን ብለን በዘጠኝ ወር 32ሺ ቶን ማቅረብ ችለናል:: በሻይ ምርትም ከሁለቱ ካምፓኒዎች ሰባት ሺህ 26 ቶን እናቀርባለን ብለን አቅደን በዘጠኝ ወር ብቻ አራት ሺህ 500 ማሳካት ችለናል::

በእነዚህ ዘርፎች የተገኘው ውጤት ከእቅድ አንጻር ጥሩ ነው:: ከአምናው ጋርም ሲነጻጸር እድገት አለው:: ለምሳሌ፣ የቡና የዘጠኝ ወር አፈጻጸም ከአምና ተመሳሳይ ወር ጋር ሲነጻጸር 15ነጥብ ሰባት በመቶ እድገት አለው:: በቅመማ ቅመም ዘርፍ ከአምና ተመሳሳይ ወር ጋር ሲነጻጸር ሁለት እጥፍ ነው:: በሻይ ምርትም ከአምና ተመሳሳይ ወር ጋር ሲነጻጸር ሁለት ነጥብ ዘጠኝ በመቶ እድገት አለው:: በቀሪው ጊዜ ትኩረት አድርገን ካልሰራን እቅዱን ለማሳካት ስለምንቸገር የ90 ቀን እቅድ አዘጋጅተን ሥራ ጀምረናል::

**አዲስ ዘመን፡- በዘጠኝ ወሩ ውስጥ ምን ተግዳሮት አጋጠማችሁ? ችግሮቹን ከመሻገር አኳያስ በምን መልኩ ሰራችሁ?**

**አቶ አስራት፡-** ከላይ የተጠቀሱትን ስራዎች ስናከናውን ሁሉ ነገር አልጋ በአልጋ ነበር ማለት አይደለም:: በርካታ ተግዳሮቶች ነበሩ:: በተለይም ሶስቱን ስትራቴጂክ ምርቶች በተሳካ ሁኔታ በማምረት እና ወደ ገበያ እስከ ማቅረብ ባለው ሂደት በርካታ ችግሮች አጋጥመውናል::

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ተጠየቅ

## “ባለሥልጣኑ - በዓለም አቀፍ ደረጃ ድርሻውን...

ከገጽ 6 የዞረ

ከእነዚህ መካከል የኤክሴሽን ስርአቱን ማጠናከር አንደኛው ነው:: ከዚህ አንጻር ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ ያለውን መዋቅር የተጠናከረ ባለመሆኑ በተለይም ቀበሌና ወረዳ ላይ የተጠናከረ መዋቅር ባለመኖሩ ምርቶቹን በተገቢው መንገድ ለማስተዳደር አስቸጋሪ አድርጎታል:: መዋቅሩ በሎጅስቲክ የተደራጀ አለመሆኑ ሌላኛው ተግዳሮት ነው::

ሦስተኛ ተግዳሮት ደግሞ፣ የምርታማነት ፓኬጅ ትግበራ ላይ በተለይ በጉንደላ ያረጀ ቡናን አለማደስ፣ የኮምፖስት ዝግጅት እና ኮምፖስት አጠቃቀም ላይ የሚስተዋሉ አንዳንድ የአመለካከት ችግሮች አሉ:: በተጨማሪም የምርት ዝግጅትና ግብይት አካባቢ ላይ የሚስተዋሉ በተለይ የምርት ጥራትን አስጠብቆ ከመሄድ አንጻር፤ ህገ ወጥ የምርት ዝውውርን መግታት አለመቻል፤ ከግብይት ሥርዓቱ አንጻር የሚስተዋሉ ችግሮች አሉ::

ከቡና አንጻር መሰረታዊ የሆኑ ችግሮችን የውስጥ እና የውጭ ብለን የለየናቸው አሉ:: የዓለም የቡና ገበያ ዋጋ መዋዠቅ ጋር ተያይዞ 2015 ዓ.ም የምርት ዘመን የነበረው እስከ 2016 ድረስ መዝለቁ በራሱ ያሳደረው ተጽእኖ አለ:: በኒዮርክ ገበያ የቡና ዋጋ በወረደ ቁጥር የእያንዳንዱን አርሶአደርና ነጋዴን ቤት እያንኳኳ ነው::ይህ አንዱ መሰረታዊ ችግር ሆኖ ቀጥሏል::

ሌላው ገበያ ከማግኘት አንጻር በተለይ አልሚ እና ላኪ አርሶ አደሮች ገዥ ከማግኘት አንጻር በወቅቱ ገዥ አለማግኘት፤ ከዋጋም አንጻር አንዳንዴ ዋጋን ከፍ አድርጎ ገዝቶ የዓለም ዋጋ በሚወርድበት ጊዜ በወረደ ዋጋ ለመሸጥ ስለሚቸገሩ ምርቱን የመያዝ እና በህገ ወጥ መንገድ ለመሸጥ ሙከራ ሲደረግ ይስተዋላል:: እንደ ክልል ውጤታማ ስራዎችን ለማከናወን እነዚህን እና መሰል ችግሮች በየጊዜው እየተከታተሉ መቅረፍ በሚል ገምግመን የተለያዩ ስራዎችን እያከናወንን ነው::

በተጨማሪም በፌዴራል ደረጃ ለውጡን ተከትሎ ቡና ላይ ያሉ ችግሮችን ለማስቀረት በቡናና ሻይ ባለስልጣን አጠቃላይ ሪፎርሞችን አድርጓል:: ሪፎርም ከተደረገባቸው ዘርፎች መካከል የግብይት ሥርዓቱ አንዱ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- የግብይት ሥርዓቱ ላይ ያለውን ችግር ከማቃለል አኳያ ለውጡን ተከትሎ የተፈጠረው የቀጥታ ግብይት ሥርዓት ምን ምን ውጤት አስገኘ?**

**አቶ አስራት፡-** ከዚህ በፊት ቡና ይሸጥ የነበረው በኢትዮጵያ ምርት ገበያ (ኢሴክስ) ነበር:: ቡና ኢሴክስ ውስጥ ገባ ማለት በገበያው ገዥ እስከሚገኝ ድረስ ቡናው መጋዘን ውስጥ ይቆያል:: ይህ ደግሞ ብዙ ችግሮች ያሉበት ነው በሚል ተገምግሟል:: ለውጡን ተከትሎ ከቡና የግብይት ሥርዓት ጋር ተያይዞ ሁለት መሠረታዊ ችግሮች ተለይተዋል::

ከተለዩት ችግሮች አንዱ ሀገራችን ከፍተኛ ምርት ያላት ሆና ወደ ውጭ ልካ በምንዛሬ የምታገኘው ገንዘብ ግን ትንሽ ነው የሚል ነው:: በሁለተኝነት የተለየው ችግር ደግሞ በንግዱ ያሉ ተዋንያንን የሚፈጥሯቸው ቢሮክራሲዎች ናቸው::

ይህን ተከትሎ በለውጡ አማራጭ የግብይት ሥርዓቶች መኖር አለባቸው የሚል ውሳኔ ላይ ተደርሶ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ (ኢሲኤክስ) አንደኛው አማራጭ የሚሆንበትን እና የቀጥታ የገበያ ትስስር ደግሞ ሌላኛው አማራጭ እንዲሆን ውሳኔ ላይ ተደርሷል:: ነገር ግን በቀጥታ ትስስር ቡናን ማገበያየት የሚቻልበትን እና አምራቾችን ከላኪዎች በማገናኘት ያለ ምንም ቢሮክራሲ በቀጥታ ወደ ማዕከላዊ መጋዘን ይገባል:: ወደ ውጭም ይላካል::

በዚህ አሰራር በተለይም በ2013 ዓ.ም የምርት ዘመን በከፍተኛ ደረጃ ቡናን ወደ ውጭ ገበያ መላክ አስችሏል:: ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ነጥብ 43 ቢሊዮን ዶላር ከግብርና ምርቶች በተለይም ከቡና ያገኘችበት ወቅት ነበር:: ይህም አንድ የለውጡ ውጤት ተደርጎ የሚወሰድ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- በቀጥታ ትስስር በሚደረገው ግብይት የቡና ላኪዎች ለአምራቾች እና ነጋዴዎች በወቅቱ ገንዘባቸውን እየከፈሉ አለመሆናቸው ይነገራል:: በዚህ ላይ የእርስዎ እይታ ምንድን ነው?**

**አቶ አስራት፡-** በቀጥታ ትስስሩ አንዱ የሚስተዋለው ችግር አምራቹ እና ላኪው ውል ገብተው ቡናውን ከተረካከቡ በኋላ ላኪው በወቅቱ ለአምራቹ ገንዘብ ያለመክፈል ይስተዋላል:: ይህ ደግሞ በአምራቹ ላይ ከፍተኛ ችግር የፈጠረ እና ነጋዴዎችንም ከገበያ እያስወጣ ነው::

አዲስ ዘመን፡- በቀጥታ ትስስሩ የሚሸጥ ቡና ደረጃ እና ሰርተፍኬት ይሰጠዋል:: ነገር ግን እነዚህን ስራዎች ለማከናወን እንደ ሀገር ያሉ ማዕከላት ትንሽ በመሆናቸው በግብይት ሥርዓቱ ላይ ችግር እየተፈጠረ መሆኑ ይነገራል:: በዚህ ላይ የእርስዎ እይታ ምንድን ነው?

አቶ አስራት፡- በቀጥታ ትስስር ቡና የሚሸጠው ተቀምሶ እና ደረጃ ወጥቶለት ነው:: ደረጃ ማውጣት እንዲቻል የቡናና ሻይ ባለስልጣን ቀደም ሲል በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከነበሩት ላቦራቶሪዎቹ በተጨማሪ በጅማ እና ሀዋሳ ሌሎች ማዕከላትን ከፍቷል:: ይሁን እንጂ እነዚህ ማዕከላት አሁንም በቂ ባለመሆናቸው ቡና ጭነው የሚሄዱ ተሽከርካሪዎች የጫኑት ቡና ደረጃ እስከሚወጣለት ድረስ ለበርካታ ቀናት እና ሳምንታት ወረፋ እንዲጠብቁ ተገድደዋል:: ይህም ነጋዴዎችን ላልተገባ ወጪ ዳርጓቸዋል::

እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ በኢትዮጵያ ቡናና ሻይ በኩል በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛል:: ከነዚህም ውስጥ አሁን ላይ በቦንጋ የደረጃ እና ሰርተፍኬሽን ማዕከል ስራዎችን ለመጀመር ቅድመ ሁኔታዎች ተጠናቅቀዋል:: በቅርቡ ሥራ ጀምራል:: ቦንጋ ላይ ያለው ማዕከል ሥራ ሲጀምር ለደቡብ ምዕራብ ሕዝቦች ክልል ቡና አምራቾችን እና ነጋዴዎችን ከከፍተኛ እንግልት እና የገንዘብ ወጪ የሚታደግ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- በክልሉ ሲለማ ከሚችለው መሬት እስካሁን ምን ያህል ለምቷል?**

**አቶ አስራት፡-** ቅመማ ቅመምን ስንመለከት በአነስተኛ ደረጃ ሴቶች በጓሮ ከሚያለሙት ጀምሮ በከፍተኛ ደረጃ ተደራጅተው የሚያመርቱ አሉ:: በስድስት ዞን ውስጥ 41 የገጠር ወረዳዎች ላይ ቡናና ቅመማ ቅመም ይመረታል::

ሻይ በከፋና በሸካ ዞኖች እየለማ ነው:: ከቆላ እስከ ደጋ ድረስ ለአካባቢው የሚስማማ ዘር በማዘጋጀት ከ489 ሺህ ሄክታር በላይ ሊለማ የሚችል መሬት አለ:: ሆኖም እስካሁን በቡና እና በቅመማ ቅመም ዘርፍ ሊያለማ የገባው 237 ባለሀብት ነው:: በዚህም 59 ሺህ ሄክታር ለምቷል:: አሁንም ተጨማሪ ባለሀብት ገብቶ ሊያለማ የሚችልበት ቦታ አለ::

**አዲስ ዘመን፡- ከቡና በተጨማሪ የቡናን ቅጠል ወደ ውጭ በመላክ ከፍተኛ ገቢ የሚያገኙ ሀገራት አሉ:: ከዚህ አንጻር ክልሉ ያለው ዝግጅት ምን ይመስላል?**

**አቶ አስራት፡-** በቡና ሽያጭ አዋጁ 1051 መሰረት ወደ ገበያ ሊቀርቡ ከሚችሉ የቡና ምርቶች ውስጥ አንዱ ቡናው ቅጠል ነው:: ቅጠሉን ወደ ገበያ ማስገባት እንደሚቻል በአዋጁ ተቀምጧል:: ነገር ግን የቡና ቅጠል ንግድ ያልተለመደ በርካታ ፈተናዎች ይኖሩታል::

ቡና አረንጓዴ ተክል ነው:: በመሆኑም ምግቡን የሚያዘጋጀው በቅጠሉ ነው:: ቅጠሉን ወደዛ ሽያጭ ከተገባ ምናልባት ወደ ፍሬው የሚሄደውን ነገር በመግታት ወደ አልታሰበ ነገር ይወስዳል የሚል ስጋት አለ:: ይሄንን እንዴት እናድርግ የሚለውን መመካከር ይፈልጋል:: በሌላ በኩል ቡና ሲያረጅ እና ምርት ሲያቆም ቅጠሉ ቢሸጥ ከፍተኛ ጥቅም ማስገኘት የሚችል ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ቡናና ሻይ ባስልጣን ተጠሪነቱ ለግብርና ሚኒስቴር በመሆኑ እና የሚተዳደረው በሲቪል ሰርቪስ ህግ በመሆኑ ምን ተግዳሮት እየገጠመው ነው?**

**አቶ አስራት፡-** በሲቪል ሰርቪስ ህግ በመተዳደሩ ከሰራተኛ ጋር በሚገናኝ የራሱ ተጽእኖ ይኖረዋል:: ለቡናና ሻይ ባለስልጣን የተሰጡት ምርቶች ለየት ያለ ባህሪ ያላቸው ናቸው:: አንደኛ ከሌሎች ሰብሎች በባህሪያቸው የተለዩ ናቸው:: ምርቶቹ በስፋት የሚመረቱ በመሆናቸው ለገበያ ካልሆነ በስተቀር ለቤት ፍጆታነት ተጠቅምን የምንጨርሳቸው አይደሉም:: ገበያ ተኮር ናቸው:: የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ሳንባም ናቸው:: ለምሳሌ፣ ሻይ ሌሎች እንስሳቶች እንኳን አይጠቀሙትም::

ሻይ እስከ 70 አመት የሚቆይ ሲሆን፤ ቡና ደግሞ ከ30 እስከ 40 አመት መቆየት የሚችል ነው:: እነዚህ ምርቶች እሴት እየጨመሩ ገበያ ለማምጣት ፕሮፌሽናል የሆኑ ሰዎችን እና ሎጅስቲክስ ይፈልጋል:: ህግና ደንብ ሲወጣም ቢሮክራሲ ያልበዛበት መሆን አለበት:: ምክንያቱም ከዓለም አቀፍ ገበያ ጋር ነው የሚወዳደሩት:: ስለሆነም ከቡና እና ሻይ ጋር ተያይዞ የዓለምን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ፈጣን ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል::

ፈጣን ምላሽ ለመስጠት መዋቅሩ ራሱን የቻለ ሆኖ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚኒስቴር የሚመራ ቢሆን ይመረጣል:: ነገር ግን ተጠሪነቱ ለግብርና ከሆነ ብዙ ጉዳዮችን አልፈህ መወሰን አትችልም:: ከዚህ አኳያ ከምርቶቹ ባህሪ እና አስተዋጽኦ አንጻር ማየት እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ላይ ድርሻውን መወጣት የሚያስችል አደረጃጀት ቢፈጠርለት ጥሩ ነው ብለን እናምናለን:: ነገር ግን በሲቪል ሰርቪስ መመራቱ አይደለም ችግሩ ተጠሪ ተቋም በመሆኑ ውሳኔ ሰጪው አካል ሌላ መሆኑ ነው::

አዲስ ዘመን፡- በምርምር የተደገፉ ስራዎችን በማከናወን ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ተባብሮ ከመስራት አንጻር ያላችሁ ተሞክሮ ምን ይመስላል?

አቶ አስራት፡- ከበርካታ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የተለያዩ የምርምር ስራዎችን በጋራ እንሰራለን:: ነገር ግን እስካሁን ቅንጅት ከመፍጠር አንጻር ገና ብዙ የተጠናከረ ነገር የለም:: ወደፊት በምርምር የተደገፉ ስራዎችን በማከናወን ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ተባብሮ ለመስራት የሚያስችሉ አሰራሮችን እየዘረጋን ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ክልሉ ከቡና እና ሻይ እንዲሁም ከቅመማ ቅመም ምን ያህል ገቢ አገኘ? የገበያ መዳረሻዎቹስ የት ነው?**

**አቶ አስራት፡-** ምርቶቹ የት ነው የሚላኩት? የሚለውን መረጃ ማግኘት የሚቻለው ከፌዴራል የቡናና ሻይ ባለስልጣን ነው:: ይሁን እንጂ አብዛኛውን ጊዜ የክልሉ ቡና የሚላከው ወደ አሜሪካ፣ ጀርመን እና አረብ ሀገራት መሆኑን የተለያዩ ሰነዶች ያሳያሉ:: ከገቢ ጋር ተያይዞ በዚህ ዓመት ከ192 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል::

**አዲስ ዘመን፡- ህገ ወጥ የቡና ነጋዴን ለመቆጣጠር በተጨባጭ ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ አስራት፡-** በብዛት ህገ ወጥ ንግድ የሚበዛው ቡና ላይ ነው:: ለዚህም የዓለም ገበያ መዋዠቅ ዋነኛ ምክንያት ነው:: ከቡና ንግድ ጋር ተያይዞ በርካታ ፈተናዎች ያሉበት ነው:: እነዚህን ችግሮች ለማቃለል እንደ ክልል ብዙ ስራዎች ተሰርተዋል::

ከኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ጋር በመቀናጀት ከፍተኛ ቡና አምራች ከሆኑ ዞኖች ጋር በመሆን ከፍተኛ የንቅናቄ ሥራ ተሰርቷል:: እንዲሁም የቡና ምርት አዘገጃጀት እና ግብይት ሥርዓት ላይ የቡና ኢንዱስትሪዎችን ማዕከል አድርገን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ሰተናል:: ከክልል ጀምሮ እስከ ቀበሌ የሚመሩበት አደረጃጀት አለ:: ይሄንን ከማደራጀት አንጻር 130 የሚሆኑ ሰዎች ያሳተፈ የንቅናቄ መድረክ አካሂደናል:: በዚህም ውጤት ተገኝቷል::

ለምሳሌ፡- እንጭጭ ቡና ሸምጥጠው በሚሸጡ ህገወጦች እስከማቃጠል የደረሰ እርምጃዎችን ወስደናል:: ለማሳያ ያህልም፣ በሸካ ዞን የኪ ወረዳ ላይ እንጭጭ ቡና ሸምጥጦ ለመሸጥ በሞከሩ አርሶአደር እና ነጋዴዎች ላይ የማያዳግም እርምጃዎችን ወስደናል:: ህገወጦች የሚያዘዋውሩትን ቡና ሸጠን ስምንት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ገቢ አድርገናል:: በቀጣይ እርምጃዎችን አጠናክረን እንቀጥላለን::

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ቃለ መጠይቅ እናመሰግናለን::**

**አቶ አስራት፡-**እኔም አመሰግናለሁ::



# ነፃ ሃሳብ

## የችግሮቻችን መሻገሪያ ብቸኛው አማራጭ

**እስማኤል አረቦ**

ኢትዮጵያ የነጻነትና የአይበገሬነት ተምሳሌት የመሆኗን ያህል፤ የጦርነት፣ የርሃብ፣ እርዛት፣ የመፈናቀልና የጥላቻ ትርክትን የያዙ ታሪኮችም ባለቤት ሆናም ትገለጻለች:: አብዛኛውን የኢትዮጵያን የውስጥ ታሪክ መለስ ብሎ ላየውም የውስጥ አለመግባባት፤ ግጭትና ጦርነት የበዛበት ነው:: በጋራ ታሪኮቻችን ላይ መግባባት ካለመቻላችንም በላይ አለመግባባቶቻችን የግጭትና የጦርነት መንስኤ እስከ መሆን ደርሷል::

ይህ ደግሞ ሀገሪቱን በማያባራ ግጭትና ጦርነት ውስጥ ከትቷታል፤ ለበርካታ ሰዋዊና ቁሳዊ ኪሳራም ዳርጓል:: ለሀገሪቱ ዕድገትም ፈተና ሆኗል:: በአንድ ሀገር ላይ ቆመን የጋራ ትርክት መገንባት አቅቶናል:: ባለፈው ታሪካችንም መግባባት ካለመቻላችንም በላይ መጪውንም ለመተንበይ አደጋች ሆኖብናል::

በተለይም የሀገሪቱ ፖለቲካ የሚመዘዘው ከኋላ ታሪካችን በመሆኑ፣ ችግሩን የበለጠ ውስብስብ አድርጎታል:: ቀደም ሲል የተሰሩ ጥፋቶችን እንደትምህርት በመውሰድ ለቀጣይ ጉዟችን ምቹ መደላድል መፍጠር ሲገባን፤ በማይቀየር ታሪክ ላይ ተጣብቀን ዛሬ እና ነጋችንን ስናበላሽ እንታያለን::

ከሁሉ የከፋው ደግሞ ያለፉት ታሪኮቻችን ላይ የሙጥኝ ብለን ስንነታረክ ዛሬ ጭምር አዲስ ቁስልና ጠበሳ እያስቀመጥን መጓዛችን ነው:: በእኛ ሀገር ብቻ የተፈጠረ በሚመስል መልኩ ከማይለውጥ ታሪክ ጋር ግብግብ ከገጠምን ዓመታት ተቆጠሩ:: ስለዚህም ከትናንት ታሪኮቻችንን ተምረን ነገን ብሩህ ለማድረግ ቆርጠን መነሳት ይጠበቅብናል::

ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ በምክክርና በመግባባት ነው:: ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባትም እንደሀገር የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ ወደ ሥራ ከገባ ከሁለት ዓመታት በላይ አስቆጥረናል:: በእነዚህ ጊዜያትም ምክክሩ የሚመራበትን አቅጣጫ ከመቀየስ ጀምሮ የሌሎችን ሀገራት ተሞክሮዎች የመቀመርና በአጀንዳ መረጣ ሂደት የሚሳተፉ ሰዎችን የመለየት ሥራዎች ተከናውነዋል::

በቀጣይም የምምክሩን አጀንዳዎች ከህብረተሰቡ የመቀበልና ምክክሩን ወደ መሬት የማውረድ ሥራዎች ይከናወናሉ:: እስካሁንም በአስር ክልሎች የተሳታፊና የተባባሪ አካላት ምርጫ አካሂዷል:: ስልጠና ሰጥቷል:: እነዚህ ስራዎች በተጠናቀቁባቸው ክልሎች ደግሞ አጀንዳ የመቅረጽ በተቀረጹት አጀንዳዎች ላይም ምክክር የማድረግ ሥራ ይከናወናል:: በሌላ በኩልም በቅርቡ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ላይ ከግንቦት 21 እስከ 27 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ አጀንዳ ማሰባሰብ ይካሄዳል:: ይህ ሂደትም ለሌሎች ክልሎች መነሻ የሚሆንና የምክክር ሂደቱንም ውጤታማነት ከወዲሁ ለመተንበይ የሚያስችል ነው::

ከሰሞኑም መንግሥትና የፖለቲካ ፓርቲዎች በቀጣይነት ምክክር የሚደረግባቸውን ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች ለመወሰን የምክክር መድረክ አካሂደዋል:: የውይይቱም ዋና ዓላማ አጀንዳዎችን ለመለየትና የምክክር ሂደቱን ለመወሰን የተካሄደ ነበር:: ውይይቱ በመንግሥትና በፓርቲዎች መካከል የትብብር ባህልን ለማጠናከርና ጤናማ የፖለቲካ ፉክክርን ለመትከል የሚያስችል ነው::

መንግሥት ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ፣ የሕግ የበላይነትን ለማስፈን፣ የፖለቲካ ሥርዓቱን ለማዘመን የሚያደርገውን ጥረት ተፎካካሪ ፓርቲዎች እንዲደግፉ ምቹ ምህዳር እንደሚፈጥርም ታምኖበታል::ይህ በጎ ጅምር ነው:: ምክንያቱም ኋላ ቀሩ የፖለቲካ ባህላችን በርካታ ችግሮችን አስከትሎብናል:: ከመነጋገር ይልቅ በር ዘግቶ መወቃቀስና አልፎ ተርፎም ነፍጥ እስከማንሳትና መገዳደል ድረስ አድርሶናል:: አሁን ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ግጭት፣ ጦርነትና መወነጃጀል ሳይሆን፤ ውይይትና ምክክር ብቻ ነው::

ስለዚህም ችግሮችን በውይይት የመፍታት ባህልም እንደሀገር ሊጎለብት ይገባል:: የስልጣኔ አንዱ መለኪያም ይኸው ነው:: በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ሥራ ውስጥም ሆነ በሌሎች መስኮች የተሰማሩ ወገኖች፣ ለውይይት ቅድሚያ መስጠት አለባቸው::

ኢትዮጵያ ከፊቷ የተጋረጡ በርካታ ችግሮች ያሉባት ሀገር ናት:: የሀገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች በሙሉ ለመነጋገርና ለመደማመጥ ጊዜ መስጠት አለባቸው:: ጽንፍ ለጽንፍ ሆኖ ቃላት መወራወርና ይዋጣልን ማለት እንደሀገር ዋጋ አስከፍሎናል:: በዚህም መንገድ ለዘመናት ተጉዘን ያተረፍነው ድህነትን፣ ኋላቀርነትና ዕልቂትን ብቻ ነው::

> የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም ወዳድ ሕዝብ ነው:: ለዘመናት አብሮ ተከባብሮ በመኖርና የሰላም ተምሳሌት በመሆን በአርአያነት ሲጠቀስ የኖረ ሕዝብ ነው

ስለሆነም የታሪካችን አንዱ ክፋይ ሆኖ ዘመናትን የተሻገረውን ጦርነትና ግጭትን ለማስወገድና የተረጋጋች፤ ሰላሟ የተጠበቀ እና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመጪው ትውልድ ለማውረስ ሀገራዊ ምክክሩ ይዞ የመጣውን ዕድል ልንጠቀምበት ይገባል::

በ2017 ዓ.ም በሀገራችን እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሀገራዊ መግባባት ተፈጥሮ ማየትን ራዕዩ አድርጎ የሚንቀሳቀሰው የምክክር ኮሚሽኑ፤ ያለፉት የታሪክ ስብራቶችን ዘግተን በአዲስ መንፈስ ሀገራችንን እንድናሻግር ጥርጊያ መንገድ የሚቀይስ ነው::

ስለዚህም ምክክሩ የቀድሞ ችግሮቻችን፤ አሁን ያሉት ችግሮቻችን መፍቻና በቀጣይም ተመሳሳይ ችግሮች እንዳያጋጥሙን የመፍትሔ አቅጣጫን የሚጠቁመን መድህን መሆኑን ማመን ይጠበቅብናል:: በሀገሪቱም መተማመን የሰፈነበት የፖለቲካ ሥርዓት ለመመስረትም እርሾ ሆኖ እንደሚያግዝ እምነት መጣል አለብን::

ሀገራዊ ምክክሩ በመሠረታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ መግባባት እንዲኖር ወሳኝ ሚና ይጫወታል:: ይህ ሊሆን የሚችለው ግን ሁሉም ዜጋ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ሲችል ነው:: የምክክር ሂደቱ የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ተሳትፎ የሚጠይቅና ውጤታማነቱም በእያንዳንዳችን አበርክቶ ላይ የሚወሰን ነው::

እያንዳንዱ ዜጋ በቅድሚያ ሁሉም ነገር በንግግር እና በምክክር ይፈታል የሚል እምነት መጨበጥ ይጠበቅበታል:: ዘመናትን የተሻገሩ ጥያቄዎችም ሆኑ እነሱን ተከትለው የመጡ አለመግባባቶች በምክክር እና በውይይት እንደሚፈቱ እምነት መጨበጥ ይገባል::

የወሰንም ሆነ የማንነት ጥያቄ እንዲሁም ራስን በራስ ማስተዳደር እና የፍትሕ ጥያቄዎች በአጠቃላይ የፖለቲካ ጥያቄዎች እና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች በሙሉ በሀገራዊ ምክክር ሊፈቱ የማይችሉበት ምክንያት አይኖርም::

አሁን ያሉት አለመግባባቶች ተወግደው በፍቃደኝነት እና በመግባባት ላይ የተመሰረተች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ምክክሩ የማይተካ ሚና አለው:: ሀገራዊ ምክክሩ ከዘመን ወደ ዘመን ሲንከባለሉ የመጡ ችግሮችን ለመፍታትና የመወያየትና የመነጋገር ባህልንም ለማዳበር ይረዳል:: በመወቃቀስ ላይ የሚያተኩረውንም የፖለቲካ ባህላችንንም ወደ መነጋገር፤ መተባበርና መደጋገፍ እንዲመጣ ያደርጋል::

ኋላ ቀሩ የፖለቲካ ባህላችን በርካታ ችግሮችን አስከትሎብናል::ከመነጋገር ይልቅ በር ዘግቶ መወቃቀስና አልፎ ተርፎም ነፍጥ እስከማንሳትና መገዳደል ድረስ አድርሶናል::አሁን ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ግጭት፣ ጦርነትና መወነጃጀል ሳይሆን ውይይትና ምክክር ብቻ ነው::

ስለዚህም ችግሮችን በውይይት የመፍታት ባህልም እንደሀገር ሊጎለብት ይገባል:: የስልጣኔም አንዱ መለኪያም ይኸው ነው:: በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ሥራ ውስጥም ሆነ በሌሎች መስኮች የተሰማሩ ወገኖች፣ ለውይይት ቅድሚያ መስጠት አለባቸው:: ሀገራዊ ምክክሩን እንደ ዕድል ሊጠቀሙበት ይገባል::

እንደ ሕዝብም የታሪካችን አንዱ ክፋይ ሆኖ ዘመናትን የተሻገረውን ጦርነትና ግጭትን ለማስወገድና የተረጋጋች፤ ሰላሟ የተጠበቀ እና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመጪው ትውልድ ለማውረስ ሀገራዊ ምክክሩ ይዞ የመጣውን ዕድል መጠቀም ሀገርን የማሻገር አንዱ ተልኮ ነው::

ስለዚህም በየትኛውም ጫፍ ያለ ኢትዮጵያዊ በዚህ የምክክር ሂደት መሳተፍና የመፍትሔው አካል መሆን ሀገርን ማዳን መሆኑን ሊረዳ ይገባል::

አካታች ሀገራዊ ምክክሮችን ማድረግ የተሻለ ሀገራዊ መግባባትን ይፈጥራል:: ኢትዮጵያውያን በዘር፤ በሃይማኖት፤ በጾታና በአካባቢያዊ ርቀት ሳይገደቡ ስለሀገራቸው መጻኢ ዕድል ሊመክሩ ይገባል:: ሀገራዊ ምክክሩ ከሞላ ጎደል ሁሉም ሃሳብ አለኝ የሚል የኅብረተሰብ ክፍል ሃሳቡን ያለምንም ገደብ የሚሰጥበትና በመደማመጥ ጉዳዮች እልባት የሚያገኙበት ይሆናል ተብሎ ይታሰባል::

የምክክር ኮሚሽኑም የተሰጠውን ጊዜ ሊያጠናቅቅ የቀረው 10 ወራት ብቻ ናቸው:: እነዚህ አስር ወራት ለኢትዮጵያውያን ወሳኝ ጊዜያት ናቸው ብሎ መውሰድ ይቻላል:: ቀሪዎቹ አስር ወራት ከፍተኛ የሆነ ሥራ የሚሰራባቸው ጊዜያት ናቸው:: እስከ አሁን የነበረው ሥራ ቢያንስ በምክክሩ የሚሳተፉ ሰዎችን የመለየት ነው::

ይህ ሂደት በራሱ እስከ ወረዳና ቀበሌ ድረስ መውረድን የሚጠይቅ በመሆኑና ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች ወደፊት ማምጣት ስለነበረብን ረዘም ያለ ጊዜን ወስዷል:: ሌላው የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወደዚህ ምክክር ማምጣቱ በጣም አስቸጋሪ ሆኖ ስለቆየ ኮሚሽኑ ሰፊ ጊዜን ወስዶበታል::

ሌላው በሀገራችን ያለው የሰላም መደፍረስ ጉዳይ ሥራው በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እንዳይሄድ እንቅፋት ሆኗል:: እስከ አሁን በትግራይ ሥራው አልተከናወነም፤ በአማራም በሚፈለገው ልክ አልተሠራም:: በመሆኑም በቀሩት ጊዜያት መሰል ችግሮችን መልክ አስይዞ በፍጥነት ሁሉም ክልሎችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ወደ ምክክር የሚመጡበትን ሁኔታ ከፈጠርን አስር ወራት ቀሪውን ሥራ ለማከናወን ያንሳል የሚባል ጊዜ አይደለም::

ጊዜ ሊወስድ የሚችለው አማራ ክልል ያለው ችግር ነው:: ነገር ግን አሁን ሥራው ተጀምሯል:: ትግራይ ክልልም እንደዚሁ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፤ በመሆኑም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተነጋግሮ መልክ ማስያዝ ከተቻለ በቀሪዎቹ አስር ወራት በጣም ብዙ ለውጥ ማምጣት ይቻላል:: በዋነኝነት ግን ችግሮቻችን በሙሉ የሚፈቱት በምክክርና በውይይት ብቻ ነው ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም ወዳድ ሕዝብ ነው:: ለዘመናት አብሮ ተከባብሮ በመኖርና የሰላም ተምሳሌት በመሆን በአርአያነት ሲጠቀስ የኖረ ሕዝብ ነው:: ከኢትዮጵያውያን ዘመን ተሻጋሪ አኩሪ መገለጫዎች መካከል የብሔር፣ የእምነት፣ የቋንቋ፣ የባህልና ሌሎች ልዩነቶችን ዕውቅና በመስጠት ተሳስቦና ተከባብሮ መኖር ትልቁ እሴት ነው:: ከዚህም አልፎ የውጭ ሀገር ዜጎች ምንም አይነት የባዳነት ስሜት ሳይሰማቸው እንደሀገራቸው እንዲኖሩ የሚፈቅድ ድንቅ ዕሴቶች ያለው ሕዝብ ነው::

ይህ አኩሪ እሴት በየዘመኑ እየተሸረሸረ ቢመጣም፣ ጨርሶውኑ ጠፍቷል ማለት አይቻልም:: በመሆኑም ኢትዮጵያዊ እሴቶች ሙሉ ለሙሉ ተሸርሽረው ከመጥፋታቸው በፊት እንደገና መመካከር ይጠበቅብናል:: ምክንያቱም ከጥንት እስከ ዛሬ የቅርብ እና የሩቅ ጠላቶች ከሀገር ውስጥ ባንዳ አሸባሪዎች ጋር ተባብረው ኢትዮጵያን ለመበታተን መሄድ እስከሚችሉት ድረስ ተጉዘዋል::

ለዘመናት አብሮ የኖረው ሕዝብን በብሔርና በሃይማኖት በመከፋፈል እርስ በእራሱ እንዳይተማመንና በሂደትም በሚኖሩ ግጭቶች ኢትዮጵያ እየተዳከመች እንድትሄድ ያለማሰለስ ሠርተዋል:: ለሀገሪቱ መድከምና በሂደትም መፈራረስ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚሉትን ኃይል በማደራጀት፤ በማስታጠቅና በማሰልጠን ታሪካዊ ጠላትነታቸውን በገሃድ ሲያስመሰክሩ ኖረዋል:: በየቦታው ነፍጥ የሚያነሱ ቡድኖችን የልብ ልብ ሰጥተው፤ አቅፈውና ደግፈው አንዳንዶችንም ለስልጣን አብቅተው ኢትዮጵያ በጊዜ ሂደት እንድትዳከምና እንድትፈራርስ በረዥሙ አልመው ሠርተዋል::

እነዚህ አካላት ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ሆን ብለው ሲሠሩ የነበሩት ኋላ ታሪክን እንደ አንድ የማጋጫ ስልት መጠቀምን ነበር:: እገሌ በእገሌ ተበድሏል፤ እገሌ እገሌን ለማጥፋት ጦር ሰብቋል፤ በርካቶችን ጨርሷል በሚል ኢትዮጵያ ከመጪው ጊዜ ይልቅ በኋላ ታሪካቸው ላይ ብቻ የሙጥኝ ብለው እንዲቀሩና ቋሚ የግጭት ምንጭ ሆኖ ሲናቆሩ እንዲቀሩ ያለመታከት ሠርተዋል::

ዛሬ ግን ሀገራዊ ምክክሩን ከችግሮቻችን መሻገሪያ ብቸኛው አማራጭ አድርገን እየተጓዝን ሲሆን፤ በዚህም በታሪክ አጋጣሚ የተፈጸሙ ስህተቶችን እንደትምህርት በመውሰድ፤ በምክክር ሀገራችንን ለማጽናት ተነስተናል:: ዳግም ሀገራችንን የበለጸገችና ገናና ለማድረግ ወደ ምክክር ገብተናል:: ይህም ይሳካል::

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

# ብልሹ አሠራርን እንደሚከላከል የታመነበት የንግዱ ዘርፍ አዲስ መመሪያ

**በኃይሉ አበራ**

መንግሥት የንግዱ እንቅስቃሴ በሕግና ሥርዓት እንዲመራ ለማድረግ የሚያስችሉ ሕጎችን በማውጣት፣ በሕጎቹ ላይም ግንዛቤ በማስጨበጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል:: አስፈጻሚው አካልም የቁጥጥርና ክትትል ሥራዎችን በአግባቡ ማከናወን እንዲችል አዋጆችን፣ መመሪያና ድንቦችን ወዘተ. በሚገባ ተረድቶ የንግድ ሥራውን በአግባቡ እንዲመራ በማድረግ ላይ በትኩረት ይሠራል:: የንግዱ ማህበረሰብም እነዚህን ሕጎች አክብሮ እንዲሠራ ለማድረግ ግንዛቤ ከማስረጽ አንስቶ፣ ቅሬታዎች ካሉትም መድረኮችን በማዘጋጀት አዳምጦ መፍትሔ የማመላከት ሥራዎችን ይሠራል::

ይህ ሁሉ ሆኖም ግን በንግድ ሥራው ላይ ክፍተቶች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፤ ሲያጋጥሙም ኖረዋል:: በአንዳንድ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት በኩል የሕግ ጥሰቶች ሲፈጸሙ፣ ሕጎች የንግዱ ማህበረሰብን አላሠራ ሲሉ፣ ተቆጣጣሪ አካላት ከሕግ ውጪ የሚሠሩበት ሁኔታ ሲያጋጥም ይስተዋላል:: ይህን ተከትሎ የንግዱ ማህበረሰብ ቅሬታዎችን ሊያነሳ፣ መንግሥትም ቅሬታዎቹን ለመፍታት የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ ይታያል:: እነዚህ ጥረቶቹ አዋጆችን፣ መመሪያዎችን እስከማሻሻል ሊደርሱ ይችላሉ::

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ በከተማዋ የሚከናወኑ የንግድ ሥራዎች ቁጥጥርና ክትትልን በተመለከተ በቅርቡ አንድ መመሪያ አውጥቷል:: ይህ የቁጥጥርና ክትትል መመሪያ የንግዱን አሠራር ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት ለማድረግ ያስችላል በሚል ታምኖበታል:: ‹‹የመንደር የንግድ ቁጥጥር የአሠራር ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 159/2016›› በሚል የተዘጋጀው ይህ መመሪያ ወደ ተግባር መሸጋገሩን ቢሮው ሰሞኑን አስታውቋል። በንግድ ቁጥጥርና ክትትል ሥራዎች ላይ ነጋዴውንም ሆነ አስፈፃሚ አካላትን ያካተተ ማሻሻያ ተደርጎ በቅርቡ ወደ ተግባር መግባቱን አመልክቷል።

መመሪያውን በተመለከተ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ በቅርቡ በሰጠው ማብራሪያ ላይ እንደተመለከተው፣ በአዲሱ የመንደር ንግድ ቁጥጥር አሠራር ሥርዓት መመሪያ ላይ የወረዳ የንግድ ቁጥጥር ባለሙያ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወስድ ሕጉ የሚፈቅድለት እስከምን ድረስ እንደሆነ በግልጽ ሰፍሯል። መመሪያው በተለይ በወረዳ ባሉ የንግድ ሥራዎች ላይ የክትትል እና የቁጥጥር ሥራ የሚያከናውኑ ባለሙያዎች አሠራር ወጥነት ባለው መልኩ እንዲመራ ያስችላል፤ ብልሹ አሠራርን ለመከላከል ያግዛል።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ የቁጥጥር ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ወይዘሪት ቅድስት ስጦታው፤ የመመሪያውን ይዘት እና አተገባበርን አስመልክቶ በተሰጠ በዚህ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ እንዳስታወቁት፤ መመሪያው ከንግድ ቁጥጥር ሥርዓት ጋር በተያያዘ አዲስ ወጥነት ያለው አሠራር ለመተግበር ያግዛል። በዚህ መመሪያ ላይ በንግድ ቁጥጥር ሥራው በየደረጃው ባሉ የአስተዳደር እርከኖች የሚወሰኑ አስተዳደራዊና ሕጋዊ እርምጃዎች በግልጽ ተካተዋል።

ምክትል ኃላፊዋ ቀደም ሲል በወጣ መመሪያ መሠረት በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን አስታውሰው፣ በሥራ ሂደትም ሲገጥሙ የነበሩ ችግሮችን ለመፍታት በሚል አዲሱ መመሪያ መውጣቱን አስታውቀዋል:: የቢሮው ባለሙያዎች በሁሉም ክፍለ ከተሞች ለቁጥጥርና ክትትል ሥራ በሚሰማሩበት ወቅት ወጥ፣ ግልጽና ፍትሐዊ በሆነ አሠራር መሥራት እንደሚያስችላቸው አብራርተዋል።

አዲሱ መመሪያ በዋናነት ሁለት ጉዳዮች ላይ ማተኮሩን ጠቁመው፤ መመሪያው በየደረጃው የሚካሄደውን የንግድ ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ፍትሐዊ፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ ያስችላል ብለዋል። ይህም የንግዱ ማህበረሰብ እንዲሁም ሸማቹ ኅብረተሰብ ከንግድ ሥርዓቱ የሚጠብቀውን አገልግሎት በተገቢው መልኩ እንዲያገኙ ታስቦ መውጣቱን ጠቅሰው፤ በዚህ ሂደት



ወይዘሪት ቅድስት ስጦታው



አቶ መስሰ ተገኑ

ውስጥ የሚፈጠሩ ሕገወጥ ድርጊቶችን ለማረም እንደሚያስችል ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በሁለተኛነት ደግሞ በሁሉም ክፍለ ከተሞች እና ወረዳዎች ባሉ የመንግሥት መዋቅሮች ተጠያቂነት ያለበት የክትትል እና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ አዲሱ መመሪያ ወጥቷል:: መመሪያው በንግድ ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓቱ ውስጥ ይስተዋሉ የነበሩ ክፍተቶችን በአሠራር ለመድፈንና ከማእከል እስከ ወረዳ ባሉ የንግድ ዘርፎች የሚካሄዱ የንግድ ቁጥጥር ሥራዎችን ወጥነት ባለው መልኩ ለማካሄድ ይረዳል።

በመመሪያው መሰረት በወረዳዎች ደረጃ የሚካሄድ የንግድ ቁጥጥርና ክትትል ሥራ ወረዳዎች የንግድ ድርጅቶችን ቁጥር፣ የቆዳ ስፋትና የባለሙያዎችን ቁጥር ታሳቢ ባደረገ መልኩ በመንደር በመከፋፈልና ከሁለት እስከ ሦስት የሚደርሱ የወረዳ የቁጥጥር ባለሙያዎችን በመመደብ ይተገበራል።

እንደ ምክትል የቢሮ ኃላፊዋ ማብራሪያ፤ ከዚህም ባሻገር መመሪያው የወረዳ የንግድ ቁጥጥር ባለሙያዎች ከንግድ ጥፋቶች ጋር በተያያዘ ለቅርብ ኃላፊዎቻቸው በጽሑፍ በማሳወቅ ከጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ማሸግ ድረስ የሚወስዷቸው አስተዳደራዊ እርምጃዎች በሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ እንዲገደቡ ተደርገዋል፤ እነዚህ ጉዳዮችም የንግድ ፈቃድ ሳይኖራቸው ሲነግዱ በተገኙ እንዲሁም ባልታደሰ፣ በታገደ ወይም በተሰረዘ የንግድ ፈቃድ ሲነግዱ የተገኙ የንግድ ድርጅቶችን የተመለከቱ ብቻ መሆናቸውን መመሪያው በግልፅ አስፍሯል።

ይሁንና የወረዳ የንግድ ቁጥጥር ባለሙያዎች በቁጥጥርና ክትትል ወቅት በሚደርሱባቸው ሌሎች ጥፋቶች ላይም እርምጃ መውሰድ ሳይኖርባቸው ጥፋቱን በጽሑፍ ለወረዳቸው ንግድ ጽ/ቤት ኃላፊ የማሳወቅ፣ ኃላፊውም ለክፍለ ከተማ ንግድ ጽ/ቤት ጥፋቱን በግልፅ ጠቅሶ ሪፖርት የማድረግ፣ በተመሳሳይም የክፍለ ከተማው ንግድ ጽ/ቤት ለቢሮው በጽሑፍ ሪፖርት በማድረግና ጥፋቱን በማሳወቅ ከቢሮው በሚሰጠው የውሳኔ ሃሳብ መሠረት ተግባሪያዊ እንዲደረግ ለወረዳው የማሳወቅና አፈጻጸሙንም የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት ይኖርበታል።

ከዚህ በተጨማሪ መመሪያው ከከተማዋ የንግድ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የንግዱ ማህበረሰብ ጥቆማ ማቅረብ የሚችልበት እንዲሁም በደረጃው በሚተላለፉ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታዎች ካሉት ቅሬታዎቹን በወረዳ፣ በክፍለ ከተማና በማዕከል ደረጃ በማቅረብ ምላሽ ማግኘት የሚያስችለው የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓትንም አካትቷል።

በመሆኑም ቢሮው ወደ ተግባር ያሸጋገረው ‹‹በመንደር የንግድ ቁጥጥርና ክትትል አሠራር ሥርዓት መመሪያ 159/2016›› ያስቀመጣቸውን ዓላማዎች ለማሳካትም የንግዱ ማህበረሰብ በአንድ በኩል የንግድ ተግባሩን በተረጋጋ መንፈስ ለማከናወን በሌላም በኩል በመመሪያውና በሌሎች የንግድ ሕጎች የተቀመጡ ግዴታዎቹን በአግባቡ መወጣት እንዲችል እንዲሁም ሙብቶቹ ሳይሸራረፉ እንዲከበሩ ለማስቻል በመመሪያው ላይ የተሟላ ግንዛቤ ሊጨብጥ ይገባል።

መመሪያው ዋና ዋና ጉዳዮችንም ያካተተ ነው፤ የፀና የንግድ ፍቃድ ስለመኖሩ፣ የዋጋ ዝርዝር ስለመለጠፉ እና ሌሎች ተያያዥ የሆኑ 25 ያህል ጉዳዮች/ ኤሌመንቶች/ የተካተቱበት መሆኑ በመግለጫው ተጠቁሟል። ተግባራዊነቱም ላይ ስምሪት የሚሰጠው በየመንደሩ በብሎክ አደረጃጀት ባለሙያ ተመድቦ ሲሆን፣ ሌላው መንገድ ደግሞ ማንኛውም ጥቆማ በሚሰጥበት ሂደት ተግባራዊ የሚሆንበት አሠራርም አለው።

በንግድ ስራ የተሰማሩ ክፍሎች የጸና ንግድ ስራ ፈቃድ ያላቸው ስለመሆናቸው ሸማቹ እንዲመለከት ለማድረግ የንግድ ፈቃዱን በግልጽ በሚታይ ቦታ ማስቀመጥ፣ የእቃዎች ዋጋ ዝርዝር መለጠፍ፣ ሸማቾች ለሚገዙት ዕቃ ደረሰኝ መስጠት በመንደር ቁጥጥር ሂደቱ ትኩረት እንደሚደረግባቸው ምክትል የቢሮ ኃላፊዋ ወይዘሪት ቅድስት አስገንዝበዋል።

የመመሪያው ክፍል ሦስት በመንደር የንግድ ቁጥጥርና ክትትል አሠራር ሥርዓት የቢሮ አደረጃጀቶች እና የቁጥጥር ባለሙያዎች ተግባር እና ኃላፊነትም እንዲሁ ይዳሰሳል። የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ የተሰጠው ስልጣን እንዳለ ሆኖ፣ ክፍለ ከተማ እና ወረዳዎችም በተመሳሳይ የሚሠሯቸው ሥራዎች እንዳሉም ተመልክቷል::

የመመሪያው ክፍል አራት ደግሞ በንግድ ድርጅቶች ላይ ጥፋት ወይም ጉድለት ሲገኝ የሚወሰዱ እርምጃዎችን አመላክቷል። መመሪያውን ከሌሎች ቀደም ሲል ከነበሩ መመሪያዎች የሚለየው የቀድሞዎቹ መመሪያዎች ወረዳ ላይ ያሉ ባለሙያዎች በሁሉም ጉብኝቶች ላይ እርምጃ የሚወስዱበት የአሠራር ሥርዓት የነበራቸው መሆኑን ምክትል የቢሮ ኃላፊዋ አስታውሰዋል።

አሁን ግን በየጊዜው የሚመጡ ጥቆማዎችን በመመሪያው አስፈላጊነት ላይ ባሉ ጉዳዮች ላይ መሠረት በማድረግ በዋናነት የፀና የንግድ ፍቃድ በሌለው ነጋዴ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ እንደሚያስወስድ ገልጸዋል። በተመሳሳይ ደግሞ ሕጋዊ እርምጃ የሚያስወስድ ተግባር መሆኑን አስረድተዋል። የፀና የንግድ ፍቃድ የሌለው ሲባል በበጀት ዓመቱ ሙሉ በሙሉ የንግድ ፍቃድ የሌለው ወይንም ደግሞ ማደስ እየተገባው ያላደሰ፣ በሥራ ላይ ሆኖ የታገደ ሆኖ የሚሠራ ሲያገኙ ለወረዳው የቅርብ ኃላፊ አሳውቆ እርምጃ ይወስዳል። በማስጠንቀቂያም እስከማሸግ ድረስ እርምጃ ይወስዳል። የደረሰበትን እርምጃ ደግሞ ለሚመለከተው የሚያሳውቅበት ሂደት ያለው መሆኑን ያስረዳሉ።

ተቆጣጣሪው ከዚያ ውጪ ያሉ ጥፋቶች ሲኖሩ ደግሞ ደረጃ በደረጃ ቁጥጥር ያደርጋል፤ ያገኘውን ግኝት ደግሞ ቅፅ 01 በሚባለው ላይ ያሰፍራል። ያሰፈረውን እና ሪፖርት ደግሞ ለጽህፈት ቤት ኃላፊው ያቀርባል። የውሳኔ ሃሳቡን ጨምሮ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑንም አስገንዝበዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በማስፈፀም ረገድ ደግሞ ስልጣኑ የተገደበበት ሂደት የለም። የተለያዩ የስነምግባር ችግር ያለባቸው ጥቂት አጥፊ ተቆጣጣሪዎችን ለማረም ግልፅ አሠራር ለማስፈን እና ወረዳ ከወረዳ ወጥ አሠራር በማስፈለጉ ጭምር መመሪያው ማስፈለጉን አመላክተዋል።

ነጋዴውም በተለያየ መንገድ ቅሬታውን ማቅረብ የሚችልበት አሠራር በመመሪያው መቀመጡን ጠቅሰዋል:: ነጋዴው ውሳኔ ከተላለፈበት በኋላ ቅሬታ ካለው በአስር ቀን ቅሬታ ማቅረብ የሚችልበት እና በአምስት ቀን ምላሽ የሚያገኝባቸው መብቶች አብረው በመመሪያ ላይ ተቀምጠዋል። መመሪያው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ሕጋዊ አሠራሩን ጠብቆ ማሻሻያዎች ሊደረጉበት እንደሚችሉም ምክትል የቢሮ ኃላፊዋ አመላክተዋል ።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ መመሪያው ሲወጣም በየደረጃው ያለውን አካል ሃሳብ ለማካተት ተሞክሯል። መመሪያው ቢሮው ከተዘጋጀ በኋላ ሕጋዊ ሂደቱን ጠብቆ በፍትህ ሚኒስቴር እንደሚዘገብ ተደርጓል፤ በመመሪያው ላይም እስከታች ያለውን ባለሙያ የማስገንዘብ ሥራም ተሠርቷል። አሁን ደግሞ መደበኛ በሆነ ሁኔታ በክፍለ ከተማ ስልጠና ጭምር በመስጠት ወደ ሙሉ ትግበራ ለመግባት ዝግጅት እየተደረገ ነው።

በቢሮው የሕግ አገልግሎት ኃላፊ አቶ መለሰ ተገኑ በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ እንደተናገሩት፤ በንግድ ሥራው ላይ ቁጥጥር ሲደረግ የቆየ ቢሆንም፣ በሂደት የታዩ ስህተቶችን ማረም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፤ ቢሮው አዲሱን መመሪያ አዘጋጅቶ በፍትህ ሚኒስቴር ክትትል እና ድጋፍ ለትግበራ ዝግጁ ማድረጉን አስረድተዋል።

አዲሱ መመሪያ በዋነኛነት ያስፈለገበት ምክንያትም በመጀመሪያ ደረጃ ብልሹ አሠራርን ለመከላከል ነው ያሉት አቶ መለሰ፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ነጋዴውም መብቱንና ግዴታውን አውቆ በተረጋጋ ሁኔታ ሥራውን እንዲቀጥል ለማድረግ ነው ብለዋል። በሌላ በኩል ደግሞ አቤቱታ እና ቅሬታ በሚኖርበት ጊዜ ቅሬታውን በማቅረብ ነጋዴው ሥራውን በአግባቡ የሚሠራበት ሁኔታ የተመላከተበት መሆኑን አስታውቀዋል።

መመሪያውን በማውጣት ሂደት በተለያዩ ጊዜያት የወጡ የንግድ ፈቃድ እና መመሪያ አዋጆችን፣ ደንብና መመሪያዎችን ለመመልከት መሞከሩ ተጠቁሟል። በእነዚህ አዋጆችና መመሪያዎች የከተማ አስተዳደሩ ንግድ ቢሮ የተሰጠው ስልጣን እና ተግባር ምን እንደሆነ ማየት ያስፈለገ በመሆኑም እነዚህን አካትቶ ግልፅ አሠራር በዝርዝር የተቀመጠበት አዲስ መመሪያ መውጣቱን አመልክተዋል። መመሪያው ወቅቱን የጠበቀና ትክክለኛ መመሪያ መሆኑን ኃላፊው ገልጸው፤ የንግዱ ማህበረሰብ መመሪያውን መሠረት በማድረግ እንዲሠራ፣ አስፈጻሚ አካላትም ተገቢው ገንዛቤ ኖራቸው ሥራውን በአግባቡ እንዲመሩ ማድረግ ላይ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

በአዲሱ መመሪያ በቢሮ ደረጃ የሚሰሩ ሥራዎች፤ በወረዳ እና በክፍለ ከተማ ያሉ የንግድ ጽህፈት ቤቶች ምን ይሠራሉ የሚለው በግልፅ ተቀምጧል። የወረዳ የቁጥጥር ሰዎች ለክትትል እና ቁጥጥር ባለሙያዎች ክትትል የሚደረግባቸውን ጉዳዮች በተመለከተ በመመሪያው ከተራ ቁጥር አንድ እስከ 25 የተቀመጡ ተግባራትን ያከናውናሉ።

የቁጥጥርና ክትትል ባለሙያዎች ቀደም ሲል ለሥራ ሲወጡ የስምሪት አሠራር አልነበራቸውም ሲሉም አቶ መለሰ ጠቅሰው፤ አሁን ግን ለሥራ ከመውጣታቸው በፊት ከኃላፊያቸው ጋር ተነጋግረው ምን ሥራ፣ የት እና መቼ እንደሚሠሩ አውቀው ቢያንስ ሁለት ወይም ሦስት ባለሙያዎች አብረው እንዲወጡ እንደሚደረግ አስታውቀዋል።

ባለሙያዎቹ የሚሄዱበት ቦታ፣ ሙሉ ስማቸው፣ የሚሄዱበት ቀን እና ሰዓት ይመዘገባል ያሉት ኃላፊው፤ ሥራቸውን አጠናቀው ሲመለሱም የሠሩትን ሥራ ለቅርብ ኃላፊያቸው የሚያስረክቡበት አሠራር ተግባራዊ እንደሚደረግ አስረድተዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ልዩነታችን ለምን ሰፋ?

**ዋስልኝ አየለ**

ልዩነት ተፈጥሯዊ ነው:: ሁሉም ሰው አንድ አይነት ምንነትና ማንነት እንዲኖረው አይጠበቅም:: እንዲያውም በሠለጠነው ዓለም ትልቁ የልዕልና መገለጫ ልዩነትን ማክበር ነው:: የሠለጠኑ ናቸው በሚባሉት የምዕራባውያን ሀገራት አንዱ መገለጫ የግለሰቦች ልዩነት መከበር ነው:: አንድ ሰው ፍላጎቱ ያዘዘነውን ነገር ሲያደርግ ማንም ከምንም አይቆጥረውም ማለት ነው:: ይህ የሰዎችን መብት ማክበር የሰው ልጅ የልዕልና መገለጫ ነው::

የእኛ የኢትዮጵያውያን ልዩነት ግን አደገኛ ልዩነት እየሆነ ነው:: የልዕልና ልዩነት ሳይሆን የጥላቻ ልዩነት፣ የመሠልጠን ልዩነት ሳይሆን የኋላቀርነት ልዩነት፣ የደግነት ልዩነት ሳይሆን የክፋት ልዩነት... እየሆነ ነው:: ልዩነት ውበት የሚሆነው የሌላውን ልዩነት (መብት ማክበር ሲኖረው ነው:: እነዚህ አደገኛ ልዩነቶች በተለይም የተማረ ነው በሚባለው የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ በስፋት እየተንፀባረቁ ነው::

ለምሳሌ፤ የዲጂታል ቴክኖሎጂ አማራጮችን የሚጠቀመው የተማረ የሚባለው ክፍል ነው:: ዲጂታል ሚዲያዎች የግለሰብ ነፃነት የሚንጸባረቅባቸው ናቸው:: አንድ ሰው በውስጡ የሚሰማውን ነገር ያለምንም ገደብ የሚናገርበት ነው:: ስለዚህ የእነዚያ ሰዎች የውስጥ እምነት ያ የሚያንፀባርቁት ነገር ነው ማለት ነው:: በሌላ ቦታ (በዋናዎቹ ሚዲያዎች፣ በስብሰባ፣ በመድረኮች...) እንደዚያ ማለት ስለማይችሉ እንጂ የልባቸው እምነት ያ ነው ማለት ነው:: ልዩነት በጣም ሲሰፋ ይከራል፣ ሲከር ደግሞ ይበጠሳል ማለት ነው::

ብዙ ጊዜ ልብ ብላችሁ ከሆነ ሁለት የኢትዮጵያ መሪዎች ፎቶ ይደረግና ‹‹ማን ይሻላል?›› የሚል ጥያቄ ይጠየቃል:: ነገርየው ለቀልድና ጨዋታ ተብሎ የሚደረግ ተራ እና ቀላል ጥያቄ ቢሆንም ግብረ መልሶች ግን የተማረ የሚባለውን ክፍል አስተሳሰብ ያንፀባርቃሉ:: ይህን ለማስተዋል የግድ በሆነ ፋውንዴሽን ወይም በዓለም አቀፍ ተቋም የሚሠራ ጥናት መጠበቅ አያስፈልግም:: ብዙዎች የውስጥ አስተሳሰባቸው በእነዚህ ቀላል ነገሮች ውስጥ ይንፀባረቃል::

መለስ ዜናዊን የሚያደንቅ ሰው ዶክተር ዐቢይን ‹‹እንዴት ከዚህ ሰይጣን ጋር ታነፃፅራለህ?›› ይላል:: ዶክተር ዐቢይን የሚያደንቅ ደግሞ መለስ ዜናዊን ‹‹እንዴት ከዚህ ሰይጣን ጋር ታነፃፅራለህ?›› ይላል:: ከሳይንስም ከሃይማኖትም፣ ከሞራልም የተጣላ የጥላቻ ሃሳብ ነው:: እንዲህ አይነት ሰው የአቶ መለስ ዜናዊን ብቃት ወይም ድክመት ከዶክተር ዐቢይ ብቃት ወይም ድክመት ጋር ማነፃፀር ስለማይችል ያለው አማራጭ ከሳይንስም ከሃይማኖትም የተጣላ የጥላቻ ስድብ መሳደብ ብቻ ነው::

ሃጫሉ እና ቴዲ አፍሮን በሙዚቃ ሥራዎቻቸው እያነፃፀረ የሃጫሉ ዜማው እንዲህ ነው፣ ግጥሙ እንዲህ ነው፤ የቴዲ አፍሮ ዜማው እንዲህ ነው፣ ግጥሙ እንዲህ ነው... ቅንብሩ ምናምን እያለ ማወዳደር አይችልም:: የሚችለው የአንደኛው አድናቂ የዚያኛውን አድናቂዎች መሳደብ ነው:: እሱ የሚያደንቀውን ቅዱስ ያኛውን ሰይጣን ማድረግ ነው:: ታዲያ ይህ ልዩነት ‹‹ውበት›› የሚባል ነው?

ይህ የትንንሽ ነገሮች የሰፋ ልዩነት ወደ ፖለቲካውም አደገ:: በፖለቲከኞች መካከል ያለው ልዩነት የሰማይና ምድር ያህል የተራራቀ ነው:: ለምሳሌ፤ በትጥቅም ሆነ በሰላማዊ መንገድ መንግሥትን የሚታገሉ ኃይሎች አሉ:: የሚገርመው ግን ከመንግሥት ጋር ካላቸው ልዩነት ይልቅ እርስ በእርሳቸው ያላቸው ልዩነት ይበልጣል:: አንደኛው ታጋይ ኃይል ቢያሸንፍ ታግሎ ከጣለው መንግሥት የከፋ ተቃዋሚና ታጋይ ያጋጥመዋል:: አንዱ ተቃዋሚ ከሌላኛው ተቃዋሚ ጋር ወደ ጦርነት የሚወስድ ልዩነት ያላቸው ናቸው:: ይህ ሁሉ ለምን ሆነ ከተባለ፤ እጅግ ኋላቀር የሆነ አመለካከት ስላለን ነው::

በሀገራችን እንደ ዕውቀት የሚታየው የግሪክ ፈላስፎችን ጥቅስ መደርደር፣ እና የተሸመደደ ‹‹ቲዎሪ›› ማነብነብ ነው:: ወደ ሥልጣኔ የሚወስደው ግን ቅንነትና የሞራል ልዕልና ነው:: አለበለዚያ የዲግሪ መዓት መደርደር፣ ከኢንተርኔት የተገለበጡ ጥናቶችን እያሳተሙ መደርደሪያ ማሞቅ ምሁር አያሰኝም::

አንዳንድ ጊዜ የሞራል ልዕልናን ልብ ብላችሁ ታውቃላችሁ? የተማረ ከሚባለው ይልቅ ፊደል ያልቆጠረው የህብረተሰብ ክፍል የተሻለ የሞራል ከፍታ አለው:: ለሠለጠነው ዓለም ሥነ ልቦና የሚቀርበው በኢትዮጵያ የተማረ ከሚባለው ይልቅ ምንም ያልተማረው ገበሬ ነው:: ለእንስሳት ሕይወት ይቆረቆራል:: የቤት እንስሳት ሲታመም ውስጡ ይረበሻል፣ የቤት እንስሳት ሲሞት ያለቅሳል:: ይህን የሞራል ልዕልና የምንሰማው የሠለጠኑ ናቸው በሚባሉት ሀገራት ነው:: የሰውን መብት አልፈው የእንስሳት መብት ተሟጋች አላቸው:: ሕይወትን ማጥፋት ነውር ነገር ነው::

ኢትዮጵያ ውስጥ ግን የተማረ የሚባለው የህብረተሰብ ክፍል ‹‹በለው! ግደለው!›› ሲል ትንሽ አይሰቀጥጠውም:: ‹‹የእነ እገሌን ዘር ማጥፋት ነው!›› እያለ የሚናገረው የተማረ የሚባለው ነው:: በዚህ ልክ ልዩነታችን ለምን ሰፋ?

የሚገርመው እኮ ደግሞ የሠለጠኑ ናቸው ከሚባሉት ሀገራት በላይ ሠብዓዊነት ያለውም ኢትዮጵያ ውስጥ ነው:: ለሞተ አስከሬን ክብር የሚሰጥበት፣ ‹‹ውሃ አይነፈግም›› የሚባልበት፣ ‹‹ቤት ለእንግዳ ነው›› የሚባልበት ባህልና ወግ ያለው ኢትዮጵያ ውስጥ ሳይሆን አይቀርም:: በአውሮፕላን አደጋ ወይም በመኪና አደጋ ሕይወታቸው ያለፈ ምንም ለማያውቋቸው ሰዎች ደረታቸውን እየደቁ የሚያለቅሱ እናቶች ያሉት ምናልባትም ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሳይሆን አይቀርም:: ሶሪያ ውስጥ ለደረሰ ዘግናኝ ጥቃት ‹‹አታሳዩኝ›› እያሉ ፊታቸውን የሚያዞሩት፣ ዓይናቸውን የሚጨፍኑት ‹‹እርም›› የሚባል የሞራል ልማድ ስላለ ነው:: የጋራ የሆነ የሰው ልጅነት ስላለ ነው:: ምንም ሰው የሌለበት አንድ ሕንጻ ቢደረመስ ምናልባትም ሳቅ ነው የሚሳቀው:: ምክንያቱም ሰው አይደለም:: ችግሩ ግን ለማያውቁት ሰው በሰውነት ብቻ የሚያለቅሱ እንዳሉ ሁሉ በሰው ሞት የሚስቁና የሚደሰቱም አሉን:: ለምን ይሆን ልዩነታችን እንዲህ የሰፋው?

በየትኛውም የሠለጠነ ዓለም ቢሆን በሰዎች መካከል ልዩነት አለ:: ልዩነቱ ግን የኢትዮጵያን ያህል የተራራቀ ነው ማለት አያስደፍርም:: ልዩነታቸው ግለሰባዊ መብትና ነፃነት ላይ፣ ግለሰባዊ ፍላጎት ላይ እንጂ ሰዋዊ ሞራል ላይ አይደለም:: በአንድ ዘፋኝና በሌላ ዘፋኝ መካከል ያለው ልዩነት ሙያዊ ልዩነት እንጂ የሰይጣንና የቅዱስነት ልዩነት አይኖራቸውም:: የግል ፍላጎታቸው የፈቀደውን ነገር ያደርጋሉ እንጂ ሌሎች ላይ ጉዳት የሚያደርስን ነገር እንደ መብት ሊያዩ አይችሉም:: ልዩነታቸው የማስተካከል እንጂ ቀዶ የመጣል ወይም ጫፉ አይነካም የሚል አይደለም:: ራሳችንን የሠለጠኑ ናቸው ከሚባሉት ሀገራት አንፃር እንየው ከተባለ በጣም የሰፋ ነው::

ልድገመውና፤ ልዩነት አይኑር አላልኩም:: ልዩነት ተፈጥሯዊ ነው:: ልዩነት ሲባል የግድ ከባህል፣ ቋንቋና ማንነት ጋር ያለውን ማለት አይደለም:: ሞራል ባለው እና ሞራለ ቢስ በሆነው መካከል ያለውን ልዩነት ማለቴ ነው:: ነውር በሚያውቅና ሀፍረተ ቢስ በሆነው መካከል ያለው ልዩነት ማለቴ ነው:: አዛኝ እና ጨካኝ በሆነው መካከል ያለው ልዩነት ማለቴ ነው:: በአጠቃላይ ሞራል ባለውና በሌለው መካከል ያለው ልዩነት ለምን ሰፋ?

# ዓለም አቀፍ



## በካንሰር ምክንያት ሕይወታቸውን ከሚያጡ ሰዎች አንድ ሶስተኛው ሴቶች ናቸው

ከሳሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ያለው የካንሰር ስርጭት በሴቶች ላይ መበርታቱን ዓለም አቀፍ የሴቶች ጤና ህብረት አመላክቷል፡፡ በአህጉሪቷ የጡት እና የማህጸን ጫፍ ካንሰር ስርጭት እያደገ እንደሚገኝ የህብረቱ መረጃ ያመላክታል፡፡ በአፍሪካ ከ60 እስከ 70 በመቶ ያሉ ሴቶች ካንሰሩ በሰውነታቸው ውስጥ ከተሰራጨ በኋላ ምርመራ የሚያደርጉ ሲሆን ከሁለት ሴቶች መካከል አንዷ ደግሞ በጡት ካንሰር እንደምትያዝ ነው የተነገረው፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ የጡት እና የማህጸን ካንሰር ከፍተኛ ስርጭት ካለባቸው 20 ሀገራት ከሳሃራ በታች ያለው ቀጣና 19ኛ ደረጃን ይዟል፡፡ በኬንያ በዓመት 7243 ሴቶች በጡት ካንሰር ሲያዙ 3ሺህ 398 ከካንሰር ጋር የተያያዙ ሞቶች ይመዘገባሉ፡፡

በአፍሪካ ሴቶች ቤተሰባቸውን እንዲሁም ሀገራቸውን በሚደግፍ ኢኮኖሚ ላይ እያደረጉት ያለው ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መሄዱን ተከትሎ ለካንሰር ህክምና እና ክትትል በነፍስ ወከፍ አንድ ዶላር መመደብ ቢቻል የሴቶችን ጤና በመጠበቅ ኢኮኖሚው ሶስት ዶላር እንዲያመነጩ ማድረግ ይቻላል ተብሏል፡፡

በአህጉሪቷ ያለው ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ እና የጤና መሠረተ ልማቶች አቅም መዳከም በጊዜ መታከም ቢችሉ የሚድኑ የካንሰር በሽታዎች በሴቶች ላይ ክንዳቸውን ማበርታታቸው ተገልጿል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ በተያዘው ዓመት ጥር ወር ላይ የዓለም ጤና ድርጅት እና ዓለም አቀፍ የሴቶች ጤና ህብረት ከዓለም ኢኮኖሚ ፎረም ጋር ካንሰርን መከላከል ዓላማው ያደረገ ጥምረት ፈጥረዋል፡፡

ጥምረቱ በተለይ በሴቶች ላይ ብቻ የሚከሰቱ የካንሰር በሽታዎችን ለመከላከል የገቢ ማሰባሰብ፣ የጤና ተቋማትን ማጠናከር፣ የገንዛቤ ፈጠራን ማከናወን ላይ ትኩረቱን አድርጎ እየሠራ ይገኛል፡፡ በአፍሪካ ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ካላቸው ሰፊ ሃላፊነት የተነሳ የግል ጤናቸውን መከታተተል እና መጠበቅ ላይ ደካማ ናቸው ያለው ጥምረቱ ይህን ለመቀየር መንግሥታት በፖሊሲ ደረጃ ሊሠሩ እንደሚገባ ነው ያሳሰበው፡፡

በእኤአ 2022 በዓለም አቀፍ ደረጃ የማህጸን እና ጡት ካንሰር ከካንሰር በሽታዎች በስርጭት መጠናቸው 4ኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ። በዚሁ ዓመት 660 ሺህ አዲስ ታማሚዎች ሲመዘገቡ 350 ሺህ ሞት አልያም 94 በመቶው ሞት የተከሰተው በደሃ እና መካከለኛ ገቢ ባለባቸው ሀገራት ነው ሲል አል ዐይን ዘግቧል፡፡

## የኬንያው ፕሬዚዳንት በግል ጄት ወደ አሜሪካ መጓዝ ‘ርካሽ ነው’ በማለታቸው ተተቹ

የኬንያው ፕሬዚዳንት ዊልያም ሩቶ ወደ አሜሪካ የተጓዙበት የግል የኪራይ ጄት ወጪ በሀገሪቱ አየር መንገድ አውሮፕላን ከመጓዝ አንጻር ዋጋው እንደሚያንስ መናገራቸው እያስተቻቸው ነው። በግል የኪራይ ጄት መጓዝ ወጪው ይቀንሳል ማለታቸው ትችት ቢያስነዝርባቸውም፣ ለጉዟቸው ምን ያህል ገንዘብ እንዳወጡ ወይም በኬንያ አየር መንገድ ቢጓዙ ኖሮ ምን ያህል ሊያወጡ እንደሚችሉ በይፋ አልተናገሩም።

ጉዳዩን በተመለከተ የፖለቲካ ተንታኙ ሔርማን ማንዮራ “ሕዝብ የሚያውቀው እውነታ ያሳሰባቸው አይመስልም” ሲሉ ለቢቢሲ ተናግረዋል። ተቃዋሚ ፖለቲከኛው ዩጂን ዋማላዋ የፕሬዚዳንቱ ንግግር “የሀገር ፍቅር የጎደለው” ነው በማለት፣ ፕሬዚዳንቱ ቢዚህ አጋጣሚ የኬንያ አየር መንገድን ማስተዋወቅ ይችሉ ነበር ሲሉ ተችተዋል።

ለሦስት ቀናት ወደ አሜሪካ ለይፋዊ ጉብኝት የሄዱት የኬንያው ፕሬዚዳንት ዊልያም ሩቶ በ15 ዓመታት ውስጥ በአሜሪካ የሥራ ጉብኝት በማድረግ የመጀመሪያው አፍሪካዊ መሪ ናቸው። ፕሬዚዳንቱ በአሜሪካ ደማቅ መንግሥታዊ አቀባበል የተደረገላቸው ሲሆን፣ ቆይታቸው በቢሊዮን ዶላሮች የሚቆጠሩ ኢንቨስትመንቶችን ለኬንያ አስገኝተዋል።

ኬንያ የሰሜን አትላንቲክ ጦር ቃል-ኪዳን ድርጅት (ኔቶ) አባል ያልሆነች አጋር የሚል ማዕረግም ከአሜሪካ አግኝታለች። ሆኖም ግን ፕሬዚዳንቱ ቅንጡ የኪራይ ጄት መጠቀማቸው እያስተቻቸው ነው። ከጉዟቸው ከተመለሱ በኋላ “የሕዝብ ንብረት ጠባቂ ነኝ” ሲሉ ራሳቸውን ተከላከለዋል።

“በአቅማችን እንድንኖር ለማድረግ ቁርጠኛ ነኝ። ያንን ለማድረግም በኬንያ አየር መንገድ ከመጓዝ ይረክሳል” ሲሉ በኤክስ ገጻቸው ላይ አስፍረዋል። የኬንያ አየር መንገድ ፕሬዚዳንቱ ያሉትን በተመለከተ አስተያየት አልሰጠም። አየር መንገዱን መጠቀም ዋጋው ይቀንሳል በሚል በስፋት እየተሰራጨ ያለውን ሐሰተኛ መረጃ ግን አስተባብሏል።

ተቃዋሚ ፖለቲከኛው ሩቶ እንዴት የግል ጄት ዋጋው እንደሚረክስ ለሕዝቡ የተሻለ ማብራሪያ መስጠት ነበረባቸው ብለዋል። ፕሬዚዳንቱ የሰዎችን “ዕይታ ከግምት ውስጥ ማስገባት



ነበረባቸው” ሲሉም አክለዋል። በሌላ ሀገር የሚተዳደር አውሮፕላን መጠቀማቸው ማኅበራዊ ሚዲያ ላይም አነጋጋሪ ሆኗል።

“ብሔራዊ አየር መንገዳችንን ፕሬዚዳንታችን አለመጠቀማቸው ያሳፍራል” ሲል አልኑር መሐመድ የተባለ ኬንያዊ ቁጣውን ገልጿል። የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙኃን፣ ለፕሬዚዳንቱ ሠራተኞቻቸው የወጣውን የግል የኪራይ ጄት ወጪን በማስላት የኬንያ አየር መንገድን መጠቀም ዋጋው እንደሚቀንስ ዘግበዋል።

ፕሬዚዳንቱ የተጓዙት በዱባዩ ሮያልጄት ነው። አብረዋቸው 30 ሰዎች ተጉዘዋል። ይህ ጄት አንድ ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር ያስወጣል። በኬንያ አየር መንገድ ቢዝነስ ክፍል ለመጓዝ የሚያስፈልገው 300 ሺህ ዶላር ነው። ሩቶ ለቪኦኤ በሰጡት ቃለ ምልልስ ለጉዟቸው ወጥቷል የተባለው ገንዘብ “የተጋነነ ነው” ሲሉ አስተባብለዋል።

ፕሬዚዳንቱ ምን ያህል ገንዘብ እንዳወጡ ሲጠየቁ በቀጥታ ባይመልሱም “ስለማወጣው ወጪ ጠንቃቃ ነኝ” ሲሉ መልሰዋል። የመንግሥት ቃል አቀባይ አይዛክ ማዋውራ ለቢቢሲ “የጉዞው ዓላማ የበለጠ ዋጋ አለው” ሲሉ ከወጪው በላይ የፕሬዝዳንቱ ጉብኝት ከፍተኛ ጥቅም እንዳለው ተናግረዋል።

በኬንያ መሠረታዊ መገልገያዎች ላይ የተጣለው ግብር ከፍተኛ ሆኖ ለባለሥልጣናት ቅንጡ ኑሮ እየዋለ ነው የሚል ትችት ሲሰነዘር ቆይቷል። ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ ሥልጣን ከያዙ በኋላ ወደተለያዩ ሀገራት 50 ጉብኝት አድርገዋል። ይህም በሦስት ወር አንዴ ይጓዛሉ ማለት ነው። መንግሥት እነዚህ ጉዞዎች አስፈላጊ እንደሆኑ እና ወጪ ለመቀነስ ውሳኔ እንደተላለፈ ገልጿል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

# ለብዙዎች የዓይን ብርሃን መመለስ ምክንያት የሆኑት ሐኪም



ክብረአብ በላቸው

የምሁር ዕውቀት የሰዎችን ኑሮና አኗኗር ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሻሻል የራሱን አስተዋፅኦ ማበርከት እንዳለበት ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ በእያንዳንዱ የዕውቀት ዘርፍ የሚደረግ ጥናትና ምርምር የሰዎችን ሕይወት በማሻሻል ላይ ማዕከል ያደረገ መሆን እንዳለበትም እንዲሁ፤ ስለዚህ አንድ ሰው በትክክል "ምሁር" ለመባል ብቁ የሚሆነው ዕውቀቱን ከራሱ አልፎ በሌሎች ሕይወት ላይ ለውጥና መሻሻል ለማምጣት የሚጠቀምበት ከሆነ ነው፡፡ ምሁርነትም ከዚህ አንፃር ታይቶና ተመዝኖ የሚሰጥ ክብር እንደሆነ ብዙዎች ይናገራሉ።

ለዚህ ቃል ብቁ ሆነው የተገኙ ጥቂት የሚባል ቁጥር የሌላቸው በስራና በሙያቸው ለበርካታ ኢትዮጵያውያን ችግር መፍትሔ ይዘው በመምጣት መድረስ የቻሉ ዕንቁዎች አሉ። ከእነዚህም የሀገር ባለውለታ ግለሰቦች መካከል በመላው ኢትዮጵያ በመዘዋወር የዓይን የህክምና አገልግሎት በመስጠት የሚታወቁት ዶክተር ጌትነት ንጉሴ አንዱ ናቸው፡፡

ዶክተር ጌትነት ንጉሴ ባለፉት 30 ዓመታት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በመዘዋወር የዓይን ብርሃናቸውን ያጡ ወገኖቻቸውን ብርሃን በመመለስ ሙያዊ ግዴታቸውን የተወጡ ሰው ናቸው፡፡ ከልጅ እስከ አዋቂ፤ ከሀብታም፣ እስከ ድሃ፣ከገጠር እስከ ከተማ፤ ከአርሶ አደር እስከ ነጋዴ፤ ከሙስሊም እስከ ክርስቲያን ወዘተ ዶክተር ጌትነት ሁሉንም አይነት ወገኖቻቸውን በነፃ በማገልገል የዓይን ብርሃናቸውን መልሰዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ አካባቢ የተወለዱት የ53 ዓመቱ ሐኪም ዶክተር ጌትነት የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በፈለገ ህይወት፤ በየካቲት 23 እና ከዚያም በኮልፌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው የተማሩት፡ ፡ ከትምህርት ቤቱ ጎበዝ ተማሪዎች መካከል አንዱ የነበሩት ዶክተር ጌትነት፤ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ነጥብ አምጥተው የህክምና ትምህርት ለመማር አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በመግባት ከ7 ዓመታት በኋላ በጠቅላላ ሐኪምነት ተመርቀዋል፡፡

የመጀመሪያ የሥራ ዓለምን የተቀላቀሉት በመርሀ ቤቴ አለም ከተማ ነበር፤ አዲስ አበባ ለዚያውም መርካቶ አካባቢ ተወልዶ ላደገና ከከተማ ወጥቶ ለማያውቅ ሰው አለም ከተማን በቀላሉ መልመድ ከባድ ነበር። መብራትና ውሃ እንደ ልብ ባልነበረባት አለም ከተማ በየጊዜው የሚመደቡ ሀኪሞች አይበረክቱባትም ነበር፤ ዶክተር ጌትነትም ተመድበው እንደሄዱ የአካባቢው ሽማግሌዎች እንደ ሌሎች ሀኪሞች ተማረው ለቀው እንዳይሄዱ ፕሮግራም አዘጋጅተው ነበር የተቀበሏቸው፤ እየዋለ ሲያድር የእዚያ ገጠር ሕዝብ ችግርን በሙያቸው መጋፈጥ ጀመሩ።

ለራሳቸውም ቃል ገቡ፤ ለ3 ዓመት በአለም ከተማ ሲቆዩ የአካባቢውን ህብረተሰብ ባህል አጠኑ፤ እንደ ባህል ከተያዙ ጉዳዮች መካከል ልጆችን ክትባት ማስከተብ አልተለመደም፤ ዶክተር ጌትነት ቦታው ላይ ሲሄዱ በአካባቢው ከሚወለዱ ሕፃናት 36 ከመቶ ብቻ ነበሩ የሚከተቡት፤ ይህንኑ ችግር በመመልከት «ሜንሽን ፎር ሜንሽን» ከተባለው የጀርመን ድርጅት ጋር በመተባባር ፕሮጀክት በመቅረፅ የአካባቢውን የክትባት መጠን ‹ከ36 ከመቶ ወደ አንድ መቶ ከመቶ አደርሰዋለሁ› ብለው ለክልሉ ጤና ቢሮ እቅድ አስገቡ፤ የክልሉ ሰዎች ‹ሊሆን የማይችል እቅድ!!› በሚል ስሜት ቢቀበሉትም እቅዱ ይሳካል የሚል እምነት አልነበራቸውም፤ ግን የጠየቁትን በጀት ፈቀዱላቸው፤ በዓመቱ ግን የአካባቢው ህብረተሰብ የሕፃናት ክትባት ምጣኔ 106 በመቶ መሆኑ በጥናት ተረጋገጠ፤ በወቅቱ የክልሉ አመራሮች በተገኙበት ዶክተር ጌትነት እውቅና አገኙ።

ከመርሀ ቤቴ ወደ ደብረ ብርሃን ተዛውረው ለ3 ዓመታት ያህል የሰሩት ዶክተር ጌትነት፤ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው ተወልደው በአደጉበት በአዲስ ከተማ አካባቢ የግል ክሊኒክ ከፈቱ፤ ክሊኒኩ ለበርካታ ሰዎች አገልግሎት ይሰጥ የነበረ ቢሆንም አትራፊ ሆኖ ሊቀጥል አልቻለም፤ ክሊኒኩ አትራፊ ሊሆን ያልቻለው የሚያስከፍለው ክፍያ እንደ መንግሥት ሆስፒታል በጣም አነስተኛ ከመሆኑም በላይ ቁጥራቸው ቀላል ለማይባሉ ሰዎች በየዕለቱ በነፃ ህክምና በመስጠቱ ነበር።

ክሊኒኩ ሲዘጋ ዶክተር ጌትነት ከጠቅላላ ሀኪምነት የዓይን ህክምና በመማር የዓይን ስፔሻሊስት ሀኪም ሆኑ፤ የጠፋውን የወገኖቹን ዓይን የማብራት ተግባሩን ‹ሀ› ብለው የጀመሩት ከዚያን ጊዜ ወዲህ ነው፡፡ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ያሉ የዓይን ብርሃናቸውን ያጡ ወገኖቹን ለመርዳትም ከኦርቢት ኢንተርናሽናል ጋር ይገናኛሉ፤ ኦርቢስ በገጠር አቅም ለሌላቸው ሰዎች በነፃ የዓይን ህክምና ይሰጥ ስለነበር ለዶክተር ጌትነት ዓይን የማብራት ፍላጎታቸውን አሳካላቸው።

የመጀመሪያ ጉዟቸው ወደ ወልቂጤ ነበር፤ የ300 ሰዎች ዓይን ቀዶ ጥገና በማድረግ ብርሃናቸውን መለሱ፤ እንደገና በወሩ እዚያው ወልቂጤ ተጨማሪ 300 ሰዎች በድምሩ ለ600 ሰዎች ህክምና አደረጉ፤ ለዓመታት ዓይነ- ስውር ሆነው በመንገድ መሪና በረዳት ተቸግረው የነበሩ ሰዎች ዓይናቸውን ታክመው ዓይናቸው ሲበራ ፊታቸው ላይ የሚያዩት ደስታ ሥራቸውን ይበልጥ እንዲቀጥሉ አደረጋቸው።

በወልቂጤ የተጀመረው የአይን ብርሃን የማብራት ህክምና ላለፉት 30 ዓመታት በመላ ሀገሪቱ በመዟዟር ለተቸገሩና ብርሃን ላጡ ወገኖች ብርሃን መሆን ችለዋል፤ ጉራጌ ዞን ቸሃ፣ ሀላባ፣ ወላይታ፣ ከምባታ፣ ሶማሌ ደገሃቡር፣ ጂግጂጋ፣ ቀብሪ ደሃር ሐረር፣ ደሴ፣ ደብረ ማርቆስ፣ ወልዲያ፣ ጎዴ፣ አሰበ- ተፈሪ፣ አሳይታ፣ አሰላ፣ ፍኖተ- ሰላም፣ ደብረ ታቦር ወዘተ የአይን ብርሃን የማብራት ሥራውን ኑሯቸውን በገጠሪቱ ኢትዮጵያ አድርገው ለብዙዎች ተስፋ ሰጥተዋል፤ በእያንዳንዱ ከተማ ከ600 እስከ 1200 ድረስ ሰዎች ህክምናውን ያገኙ ነበር።

ዶክተር ጌትነት በመጀመሪዎቹ ሁለት ዓመታት በገጠር እየዞሩ ህክምናውን ሲሰጡ ቆይተው ወደ አዲስ አበባ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ገቡ፤ የዓይን ህክምና ክፍል ኃላፊ ሆነው በአስተዳደርም በህክምና ሥራ ለ7 ዓመታት ያህል ቆዩ፤ በወቅቱ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል ለዓይን ህክምና ወደ አዲስ አበባ የሚመጡ የዓይን ብርሃን ያጡ ሰዎች በወቅቱ የሚሰጣቸው ቀጠሮ 2 ወር ከ15 ቀን ነበር፤ ዶክተር ጌትነት ክፍሉን በበላይነት መምራት ከጀመሩ በኋላ ግን ከሀኪሞች ጋር በመነጋገርና ፕሮግራም በማውጣት ዛሬ የመጣ ሰው ነገ ቀጥሮ ተሰጥቶት ታክሞ አይኑ በርቶ ወደ ቤተሰቦቹ እንዲሄድ ማስደረግ ችለዋል።

የተበላሹ የሆስፒታሉ የህክምና መስጫ መሳሪያዎችንም ከኪሳቸው አውጥተው በማሰራት የህክምና ሂደቱ እንዳይስተጓጎል ብርቱ ጥረት አድርገዋል፤ ሐኪሞች ከመደበኛ የሥራ ሰዓታቸው በኋላ በዚያው በሆስፒታሉ ውስጥ በተወሰነ የክፍያ ለውጥ ህክምና እንዲሰጡ የተደረገውም ዶክተር ጌትነት ምኒልክ ሆስፒታልን በሚመሩበት ወቅት ነበር፡፡ ሰዎችን ከማከሙ በተጨማሪ የህክምና ቡድን አደራጅተው ከላየንስ ክለብ ጋር በመተባበር ወደ ገጠር እያቀኑ የብዙዎችን የዓይን ብርሃን መልሰዋል።

ዶክተር ጌትነት የህክምና ቡድኑን ይዘው የዓይን ሞራ ህክምና ወደሚደረግባቸው አካባቢዎች የሚንቀሳቀሱት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፕሮግራም መሰረት ሲሆን፤ በመንግሥት ሆስፒታል እዚያው አካባቢ በሚገኙ ሐኪሞች በዓይን ሞራ ግርዶሽ ሳቢያ ብርሃናቸውን ያጡ ሰዎች ተመዝግበው እንዲዘጋጁ ያደርጋሉ፤ ህክምናውም የሚሰጠው በመንግሥት ሆስፒታል ውስጥ ነው፡፡

ምክንያቱ ደግሞ ከህክምናው በኋላ ክትትል የሚያስፈልጋቸውን ህመምተኞች የሆስፒታሉ ሀኪሞች እንዲከታተሏቸው እድል ይሰጣል፤ በመሆኑም ቡድኑ በቦታው ሲደርስ ተጨማሪ ምርመራ በማድረግ በቀጥታ ወደ ቀዶ ጥገናው ነው የሚገባው፤ በቀን ከ60 እስከ 80 ሰዎችን በአንድ የጉዞ ፕሮግራም እስከ 800 ሰዎችን የሚያክሙት ዶክተር ጌትነት ቀዶ ጥገና የተደረገለት ሰው ዛሬ ተሰርቶለት ነገ ዓይኑ ስለሚበራለት በሰው ድጋፍ የመጡ ሰዎች እየጨፈሩ ወደ ቤታቸው ሲሄዱ መመልከት ስራውን እንድወደው አድርጎኛል ይላሉ።

ያም ሆኖ የመንግሥት ፖሊሲ ቅድሚያ የሚሰጠው ለተላላፊ በሽታዎችና ገዳይ ለሚባሉ በሽታዎች በመሆኑ ለእንደዚህ ዓይነት የዓይን ህክምና ጉዳይ የሚይዘው በጀት በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ህብረተሰቡም የዓይን ሞራ ግርዶሽ በህክምና በቀዶ ጥገና የሚስተካከል መሆኑን ስለማያውቅ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ዓይናቸው ጠፍቶ ከምርታማነት ውጪ ሆነዋል ይላሉ።

ይህንን ችግር ለመፍታትም ከተለያዩ በጎ አድራጊ ድርጅቶችና ከለጋሾች ጋር በመተባባር መንግሥት ብሄራዊ የዓይነ-ስውርነት ማስወገጃ ኮሚቴ በመመስረት ችግሩን ለመቅረፍ ብዙ ተሞክሯል፤ የኢትዮጵያ የዓይን ህክምና ማህበር ፕሬዚዳንት ሆነው ያገለገሉት ዶክተር ጌትነት፤ በዚህ በኩል ህክምና የማግኘት እድሉ ያልነበራቸው የገጠር ነዋሪዎች ህክምናውን በነፃ እንዲያገኙና ብርሃናቸው እንዲመለስ አድርገዋል፡፡

ዶክተር ጌትነት የዓይን ብርሃን ያጡ ሰዎች ብርሃናቸው ተመልሶ ማየት ሲችሉ የሚያሳዩት ድርጊት እየማረካቸው ሲመጣ ቀዶ ጥገና የሚደረግላቸውን ሰዎች ከህክምናው በፊትና በኋላ ቪዲዮ ማስቀረፅ ጀመሩ፤ በዚህ መልክ ከሰሯቸው ከ22 ሺህ በላይ ሰዎች መካከል ከ1500 በላይ የሚሆኑ ባለ ታሪኮችን በቪዲዮ አስቀርጸው ይዘዋል፡፡ ብዙዎቹ በሰዎች ድጋፍ ሲመጡ የሚታዩ ሰዎች ቃለ- ምልልስ ሲደረግላቸው ዓይናቸው የሚበራ አይመስላቸውም፤ ህክምናው ተሰጥቷቸው ዓይናቸው ሲፈታ ደግሞ የሚታየው ሁኔታ ብዙ ጊዜ የሚያሳዝንና የሚያስለቅስ ነው፤ ዶክተር ጌትነት ህክምናውን ሰርተው ዓይናቸውን ሲፈቱላቸው በአንዳንድ ሰዎች ድርጊት አብረው ያለቅሱ ነበር።

ድምፃቸውን አጥፍተው በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እየዞሩ የዓይን ብርሃን ላጡ ወገኖቹ ብርሃን ሲሰጡ የኖሩት ዶክተር ጌትነት ልታይ ልታይ የማይሉ ብርሃናቸው በተመለሰላቸው ሰዎች ደስታ የሚደሰቱ በጎ አድራጊ ናቸው፡፡ ላለፉት 30 ዓመታት ስላከናወኗቸው የበጎ አድራጎት ተግባራትም ከ53 በላይ የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት በርካታ ምስክር ወረቀቶችና ልዩ ልዩ ሽልማቶች ተበርክቶላቸዋል።

በአይን ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በኢትዮጵያ ቢያንስ 1 ነጥብ 8 ሚሊዮን አይነ ስውራን ሰዎች ሲኖሩ ከዚህ ውስጥ ቢያንስ 50 ከመቶው ሊታከም በሚችለው በዓይን ሞራ ግርዶሽ ሳቢያ የዓይን ብርሃናቸውን ያጡ ናቸው፡፡ በዶክተር ጌትነትና ሌሎች በጎ አድራጊ ተቋማት በየጊዜው በሚደረገው በየጊዜው የዓይን ሞራ ግርዶሽ ቀዶ ጥገና ቁጥሩን ለመቀነስ ጥረት ቢደረግም ቁጥሩ እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አይደለም የሚሄደው፡፡

የዚህ ምክንያት ደግሞ ከዚህ በፊት በህክምና እጦት በአይን ሞራ ግርዶሽ ሳቢያ የዓይን ብርሃናቸውን ያጡ ሰዎች ቁጥር እንዳለ ሆኖ ከስር ከስር ደግሞ በየዓመቱ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ሰዎች የዓይን ብርሃናቸውን የሚያጡ በመሆኑ ነው። እድሜ ሲጨምር አይን በሞራ የመጋረድ እድሉ ሰፊ ስለሆነ ቁጥሩ እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ እንደማይሄድ ይነገራል።

በግላኮማ፤ በስኳር፤ በደም ግፊትና በልዩ ልዩ በሽታዎች ሳቢያ የዓይን ብርሃናቸውን የሚያጡ ሰዎች ቁጥር ከፍተኛ ነው። ያም ሆኖ በህክምና እርዳታ የዓይን ብርሃናቸውን ያጡ የዓይን ሞራ ግርዶሽ ህመም ተጠቂዎችን ዶክተር ጌትነትና የሥራ ባልደረቦቻቸው ኑሮአቸውን በገጠሪቱ ኢትዮጵያ አድርገው ብርሃን ላጡ ብርሃን እየሆኑ ነው፡፡ ከ100 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ባለባት በሀገራችን የዓይን ሐኪሞች ቁጥር ከ120 በላይ አይደለም፤ያም ሆኖ ግን በግለሰብ ደረጃ ለ22 ሺህ ሰዎች ብርሃናቸውን መመለስ የውቅያኖስን ውሃ በማንኪያ ቢመስልም ጉዳዩ የዓይን ጉዳይ መሆኑ ሲታሰብ የዶ/ር ጌትነት ጥረት ከፍተኛ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡

እኛም በዚህ ለሕዝብና ሀገራቸው መልካም ያደረጉና በተሰማሩበት ሙያና የሥራ ዘርፍ ሁሉ የማይነጥፍ አሻራ ማኖር የቻሉ ግለሰቦች ታሪክ አንስተን ለአበርክቷቸው ክብር በምንሰጥበት በዚህ የባለውለታዎቻችን አምድ እውቁን የአይን ህክምና ባለሙያ ዶክተር ጌትነት ንጉሴ ላበረከቱት ዘመን ተሻጋሪ ሥራ አመሰገንን። ሰላም!

ለዚህ ጽሑፍ በምንጭነት ተወዳጅ ሚዲያ ድረ ገፅን ተጠቅመናል።

# ስፖርት



# የኢትዮጵያውያንና ዩጋንዳውያን አትሌቶች የኦስሎ ዳይመንድ ሊግ ፉክክር

ብርሃን ፈይሳ

የአትሌቲክስ ስፖርት ቤተሰብ የነገውን የረጅም ርቀት ድንቅ ፉክክር ሊመለከት፤ የአትሌቶቹንም ብቃት ሊመሰክር ቀጠሮውን ኖርዌይ አስሎ ላይ አድርጓል:: የዳመንድሊግ ሰባተኛዋ መዳረሻ በሆነችው ኖርዌይ የሚደረገው ይህ ውድድር በሜዳ ተግባራትና በተለያዩ ርቀቶች ከሚደረጉ ሩጫዎች መካከል የተለየ ግምት የተሰጠውና ቀልብ ሳቢ ትዕይንት ይስተናገድበታል ተብሎ የሚጠበቀው የወንዶች 5ሺ ሜትር ነው:: ይህ ውድድር የላቀ ትኩረት ያሰጠው ደግሞ በምስራቅ አፍሪካውያኑ ሀገራት ኢትዮጵያ እና ዩጋንዳ የርቀቱን ምርጥ አትሌቶች በማገናኘቱ ነው::

በረጅም ርቀት አትሌቲክስ ስኬታማ የሆኑት የሁለቱ ሀገራት አትሌቶች የሚፎካከሩባቸው መድረኮች ከፍተኛ የአሸናፊነት ፍልሚያ ማስተናገዳቸው አይቀርም:: የፓሪሱ ኦሊምፒክ ደግሞ ሁለት ወራት ብቻ የቀሩት መሆኑን ተከትሎ አትሌቶቹ ያሉበትን ብቃትና ዝግጅታቸውን ለመመዘን ከማስቻሉ ባለፈ አትሌቶቹ በኦሊምፒክ የሚካፈሉባቸውን ርቀቶች በሚመለከትም ፍንጭ የሚሰጥ ነው የሚሆነው:: ተጠባቂው የነገ ውድድርም እንደ በሪሁ አረጋዊ፣ ዮሚፍ ቀጄላ፣ ሃጎስ ገብረሕይወት፣ ጥላሁን ኃይሌ፣ ጆሹዋ ቺፕቴጊ፣ ጃኮብ ጂፕሊም፣... በመሳሰሉት የአትሌቲክስ ጀግኖች መካከል የሚደረግ ነው::

በኦሊምፒክም ሆነ በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና መድረክ በዚህ ርቀት የምስራቅ አፍሪካ አትሌቶች ጠንካራ ተፎካካሪና ውጤታማ መሆናቸው ይታወቃል:: ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የኬንያ አትሌቶች ስኬት እያነሰ የአውሮፓዊቷ ኖርዌይ እየጨረ ቢመጣም የኢትዮጵያውያን እና ዩጋንዳውያን ፍልሚያ ግን በይበልጥ ሳቢ እየሆነ ይገኛል:: ዩጋንዳዊው ጆሹዋ ቺፕቴጊ ደግሞ በርቀቱ የኦሊምፒክ ቻምፒዮና ከመሆን ባለፈ በጀግናው ኢትዮጵያዊ አትሌት ቀነኒሳ በቀለ ተይዞ የቆየውን የርቀቱን ክብረወሰን በመስበር ውጤታማነቱን አስመስክሯል:: በፓሪሱ ኦሊምፒክም ይህንኑ ስኬቱን ለመድገም ያለመ ስለመሆኑ ትኩረታቸውን በአትሌቲክስ ስፖርት ላይ ያደረጉ የመገናና ብዙሃን ይጠቁማሉ:: ይሁንና በዳይመንድ ሊጉም ሆነ በኦሊምፒኩ ከወጣቶቹ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የሚገጥመው ፈተና ቀላል እንደማይሆን ነው የሚገመተው::

ባለፈው ዓመት ሉዛን ላይ አሸናፊ የነበረውና በሞናኮ ሁለተኛ የወጣው ወጣቱ አትሌት በሪሁ አረጋዊም በውድድሩ አሸናፊ ይሆናሉ በሚል ከሚጠበቁ አትሌቶች መካከል ዋነኛው ነው:: በጠንካራ አቋም የተያዘውን የውድድር ዓመት የጀመረው አትሌቱ በሰርቢያው የዓለም ሀገር አቋራጭ ቻምፒዮና እንዲሁም ባለፈው ሳምንት አሜሪካ ላይ በተሳተፈበት የ5ሺ ሜትር ርቀት ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ ማጠናቀቁ የሚታወስ ነው:: የነገው ዳመንድ ሊግ ተሳትፎውም የመጀመሪያው ሲሆን ለፓሪሱ ኦሊምፒክ እያደረገ ያለውን ዝግጅት የሚያስመሰክርበት ሩጫ በመሆኑ ለአሸናፊነት ከፍተኛ ጥረት እንደሚያደርግ ይጠበቃል::

ከዩጋንዳውያን አትሌቶች ጋር ሲፎካከር ይህ የመጀመሪያው ያልሆነው በሪሁ ፈተናእንደሚሆንባቸውም ነው የሚጠበቀው:: በተለይም በነገው ውድድር ከሚሳተፉት መካከል አንዱ ከሆነው ጃኮብ ኪፕሊሞ ጋር በዓለም ሀገር አቋራጭ ቻምፒዮና ያሳዩት የትከሻ ለትከሻ ፉክክር የሚዘነጋ አይደለም:: በእኩል የብቃት ደረጃ ላይ የሚገኙት አትሌቶቹ በሰከንዶች ብቻ የተበላለጡ ሲሆን፤ ዛሬም በመካከላቸው የአሸናፊ ተሸናፊ ፍልሚያ እንደሚስተናገድ ይገመታል::

አምና በኦስሎ ዳይመንድ ሊግ አሸናፊ የነበረው ዮሚፍ ቀጄልቻ በዚህ ውድድር ተሳታፊ መሆኑ የተረጋገጠና በድጋሚ ባለድል ይሆናሉ ተብለው ከሚጠበቁ አትሌቶች መካከል ይገኛል:: ከሁለት ወር በፊት ስፔን ላይ በ10 ኪሎ ሜትር ውድድር አሸናፊ የነበረው አትሌቱ በሌሎች ውድድሮች ላይ አልታየም:: ይኸውም ትኩረቱን በዝግጅት ላይ አድርጎ መቆየቱን የሚያመላክት ሲሆን፤ የዓምናውን ድል ለማደስ ነገ እንደሚሮጥም ነው የሚጠበቀው:: ሌላኛው ኢትዮጵያዊ አትሌት ሃጎስ ገብረሕይወትም ከተፎካካሪ አትሌቶች መካከል ይገኛል:: የ5ሺ ሜትር ርቀት አትሌቱ እአአ 2013ቱ የሞስኮ ዓለም ቻምፒዮና የብር፣ በቀጣዩ ደግሞ የነሃስ ሜዳሊያ ሲያጠልቅ፤ በ2016ቱ የሪዮ ኦሊምፒክ ደግሞ የነሃስ ሜዳሊያ ባለቤት ነበር:: ተስፈኛው አትሌት ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታት ተደጋጋሚ ጉዳት በማስተናገዱ ምክንያት ብቃቱን ለማሳየት ባይችልም በፓሪስ ኦሊምፒክ ግን ሀገሩን መወከል በሚችልበት ብቃት ለመመለስ በጥረት ላይ ይገኛል::

በዚህ ርቀት አራተኛው የዓለም ፈጣን አትሌት የሆነው ወጣቱ አትሌት ጥላሁን ኃይሌም ውድድሩን ከሚያደምቁት መካከል ተሰልፏል:: በቡዳፔስቱ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ከብሄራዊ ቡድን ምርጫ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ቅሬታ የነበረው አትሌቱ በተያዘው ዓመት ብቃቱን በማስመስከር ፓሪስ ላይ ሀገሩን ለመወከልም ይሮጣል::




**የኢትዮጵያና የጋንዳ አትሌቶች የ5ሺ ሜትር ፍልሚያ በኦስሎ ዳይመንድሊግ ትልቅ ትኩረት አግኝቷል፣**


## ለ2ኛ ጊዜ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

በአፈ/ከሳሽ- -------- ህጻን ሄኖክ ወሰን ሞግዚት ኤልሻዳይ መኮነን

በአፈ ተከሳሾች--------- 1ኛ/ አቶ ክንዱ እውኑ

2ኛ/ ቻይና ሬይልወይ

3ኛ/ ኦሮሚያ ኢንሹራንስ መካከል ስላለው የገንዘብ አፈጻጸም

ክስ ክርክር ጉዳይ የ2ኛ አፈጻጸም ተከሳሽ ቻይና ሬይልወይ ኢንጅነሪንግ ቁጥር 3 ንብረት የሆነው ባለ 8 ቤርጋ 844/ስምንት መቶ አርባ አራት ብረት የሚሸጠው በ2ኛ ጨረታ ጊዜ ከፍተኛ ዋጋ ለሚያቀርብ ተጫራች እንድሸጥ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

በመሆኑም የጨረታ ማስታወቂያው ከግንቦት 19 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ ሰኔ 04 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ለ15 ቀን ክፍት ሆኖ ቆይቶ ጨረታው ሰኔ 05 ቀን 2016 ዓ.ም ከጧቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 6፡30 ሰዓት ድረስ ጨረታው ይካሄዳል፡፡

ስለሆነም በጨረታው መሳተፍ ወይም መግዛት የምትፈልጉ በላልይበላ ከተማ መስቀል ክብራ ቀበሌ ቻይና ካምፕ ንብረቱ በሚገኝበት በመገኘት መጫረት የምትችሉ መሆኑን እያሳወቅን የጨረታ አሸናፊው የአሸነበትን 1/4ኛውን ለሃራጅ ባይ ባለሙያ ወዲያውኑ ማስያዝ ይኖርበታል፡፡

**የሰ/ወሎ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት**

## የሐራጅ ማስታወቂያ

የፍ/ባለመብት ሀይማኖት ወ/ገብርኤል እና በፍ/ባለዕዳ እነ አቶ ሀይሉ ወ/ሰንበት መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ችሎት በመ/ቁጥር 301812 በ24/10/2014 ዓ.ም እና በመ/ቁ 305112 በ13/12/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 02 የቤ.ቁ 609 በተመለከተ የሟች ወ/ሮ አዛለች ወልደየስ የውርስ ሀብት የቦታ ስፋት 123 ካ/ሜ የሆነው የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 3,232,701(ሶስት ሚሊዬን ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺ ሰባት መቶ አንድ ብር) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ሰኔ 25 ቀን 2016 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ8፡30 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያዉኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ጀምሮ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፓርት ንብረቱን ባለበት ቦታ ድረስ በመውሰድ መጐብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን መነሻ ግምት 1/4 ኛውን በንግድ ባንክ በተረጋገጠ C.P.O ማስያዝ ይኖርበታል፡፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ c.p.o የሚያመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በፍ/አ/ዳ/ስም c.P.O አሰርቶ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብቻ ሙሉ ገንዘቡን በ15 ቀን ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት የፍ/አ/ዳይሬክቶሬት ንብረቱን በህጋዊ መንገድ በሀራጅ ስለመሸጡ ለሚመለከተው አካል ማስረጃ ከመጻፍ ባለፈ ስም የማዛወር ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**